# ምዕራፍ ሁለት

## ገድለ ተክለ ሃይማኖት

በኢትዮጵያ የወንጌል ታሪክ « ተክለ ሃይማኖት» እየተባሉ የሚጠሩ መልካም የወንጌል ተጋድሎ አድርገው ያለፉ ሰው እንደነበሩ
የተለያዩ ጸሐፊዎች በጽሑፋቸው ዘክረዋቸዋል:: ( የቤተክርስቲያን ታሪክ ዮሐንስ ሳንዴቪድ )

ሆኖም በሃገራችን የቤተክርስቲያን ታሪክ ዙሪያ ከሁለት በላይ የሆኑ በተክለ ሃይማኖት ስም የሚጠሩ በመልካም ሆነ በመጥፎ ታሪካቸው የሚታወቁ ሰዎች እንደነበሩ በሰሜኑ ፣ በማዕከላዊውና በሰሜን ምሥራቁ እንዲሁም ከማዕከላዊው ጋር የሚስማማ አተራረክ ያለው በደቡቡ የሃገራችን ክፍሎች ጋር ንክኪነት ያላቸው ገድሎች ይናገራሉ::

የታሪክ መሳሳብና መናጠቅ በመኖሩ የትኛው የወንጌል ሰው ነበሩ የሚለውን ለተመራማሪዎች በመተው በአንድም በሌላ ቤተ-ክርስቲያናችንን በመጉዳት ላይ ስላለው በተክለ ሃይማኖት ስም እየተጠራ ያለውን ገድል እንመለከታለን::

ይህንን ጽሑፍ ስናዘጋጅ ሁለት ዓይነት ገድለ ተክለ ሃይማኖትና በሌሎች መጽሐፍ ላይ በተጠቃሽነት የተጠቀመ ሌላ 3ኛ ተክለ ሃይማኖት የሚባል ሰው ታሪክ ተመልክተናል:: በ3ቱም ውስጥ ካገኘናቸው ጸረ ወንጌል መልእክቶች በጥቂቱ ወስደን ሕዝብ እንዲያውቀውና ባለማወቅ እያለቀ ያለውን ወንጀል እንዲያቆምና ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ቃልና ትዕዛዝ እንዲመጣ ለመርዳት ጽፈናል::

# ተክለ ሃይማኖት የነፍሳችን መዳኛ

በተክለ ሃይማኖት መጽሐፍ መግቢያ እንዳልነው የገድል ጽሑፍ ውርርስ በመኖሩ አንደኛው ከአንደኛው ለመበላለጥ እግዚአብሔርን ክርስቶስንና መንፈስ ቅዱስን አልፎ አልፎ በመጥቀስ እንዲሁም ተክለ ሃይማኖት የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው በማለት የሚናገሩ ቃላቶች አሉበት ። ይህም መጽሐፉ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሲባል በዘዴኞች የተደረገ ጥበብ ነው።

ለነገሩ መተትንና አስማትን የሚሠሩት ሳይቀሩ በከተቧቸው ክታቦች ላይ እግዚአብሔር የሚል ጽሑፍ ያደርጉ የለ ? ሰይጣንም እኮ « እግዚአብሔር ብሎ ለመጥራት አይቸገርም » ( ዘፍ 3፥ 2) ሆኖም በገድለ ተክለ ሃይማኖት ስም የሚጠራውን መጽሐፍ ስናይ ግን በታሪክ እንደተገለጠው አንድ የወንጌል አገልጋይ ሰው እንደነበሩ የሚጠቁም ሲሆን ገድላቸውን ጻፍን የሚሉ መናፍቃን ግን ነበሩ የተባሉትን ሰው ስም በመታከክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር የቸርነት ሥራ ላይ ወንጀልን አስገብተዋል።

« ፍሥሐ ለክሙ ወረብሐ ለነፍስክሙ ወመድኃኒተ ለሥጋክሙ ወመንጽሔ ለርስሐትክሙ ... ወሥረይ ለቁስለ ነፍስክሙ » ትርጉም :- « ለእናንተ ተድላ ደስታችሁ ነውና ለሥጋችሁ መጠበቂያ ለነፍሳችሁ መዳኛ ኃጢአታችሁን የሚያነፃ ... ለነፍሳችሁ መድኃኒት » ነው ብለውታል። ( ገድ ተክ ምዕ 2፥ 14- 15 )

እውነት የሆነውና በዘመናት ሁሉ ሁሉን እያሳለፈ ያለው ከወርቅ ይልቅ የነጠረ ፈጽሞ ስሕተት የማይገኝበት ፣ የተፈራውና የሕያው አምላክ ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳችን ግን «በራሱ አሠራር የዓለምን ኃጢአት ሊያነጻ በጎ ፈቃዱ የሆነ እግዚአብሔር ከፍጡራን በአንዱ እንኳ እንዳይቻል ግን በእርሱ ብቻ እንዲቻል አውቆ ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድያ ልጁን ለዚሁ እንደላከው ይናገራል።

በተለይ ጌታችን ከሴት ከተወለዱት መካከል የሚበልጠው የለም ብሎ የተናገረለት ነቢይና መንገድ ጠራጊ መጥምቁ ዮሐንስ « ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም » ትርጉም :- « የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ » በማለት ተከታዮቹንና በወቅቱ

የሚሰሙትን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ፈቃድና ኃሳብ ዘወር እንዲሉ አድርጓል:: ( ዮሐ 1÷ 29 )

ብዙ ጊዜ እንዳልነው ያሻቸውን ለወደዱት መስጠት ባሕላቸውና ዓላማቸው በመሆኑ ይህን በእግዚአብሔር ዕቅድ የክርስቶስ ብቻ ሥራ የሆነውን ኃጢአትን የማንጻት ግብር እነርሱ ተክለ ሃይማኖት ለሚሉት ሰው ሰጥተውት ሕዝቡ የኃጢአት ሥርየት ለማግኘት ከክርስቶስ ይልቅ በተክለ ሃይማኖት እንዲያምን አድርገዋል ::

በሃገራችን የገድል ደራስያንና በብዙ የመቅደስ ሙያተኞች ዘንድ « ኢትዮጵያዊው 25ኛ ሱራፌል አንዳንዴም 25ኛው ካህን እየተባሉ የሚጠሩት ባለ 6 ክንፉ ተክለ ሃይማኖት » የገድላቸው ጸሐፊ ይህን ረስቶ « የተክለ ሃይማኖት ትውልዱ ኢየሩሳሌም ነው » በማለት ግጭቱን ጀምሯል ( ምዕ 3÷9 ገጽ 16 )

## እንደገድሉ ትረካ የተክለ ሃይማኖት ልደትና አስተዳደግ

በዚህ ታሪክ አንባቢ ልብ እንዲለው የምንፈልገው ደራሲዎቹ የጽሑፋቸው ዓላማና ግብ ምን እንደሆነ እንድናስተውለው ነው:: ታሪክ ሲጽፉ ታሪክ ታሪክን እንዲስበው በማድረግ ስለሆነ የታሪኩ ምንጭና መጀመሪያ በራሱ የሚያስተላልፈው መልእክት አለው ::

ከባለጸጋ ቤተሰብ እንደተወለዱ የሚነገርላቸው « ተክለ ሃይማኖት» እናታቸው እግዚእ ኀረያ መካን ነበረች በየወሩም በ12 የሚካኤልን በዓል እየዘከረች ትኖር ነበር ይላል ::

እግዚእ ኀረያ « ሚካኤልን» በየወሩ እየደገሰች ታከብር ነበር የሚለው ልምምድ ከየት የተቀዳ ነው ? መጽሐፍ « ቀንን የሚያከብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ያከብራል » ይላል እንጂ ለሚካኤል ለገብርኤል ወ.ዘ.ተ የሚል የለም:: እንግዲህ እግዚእ ኀረያ በመጽሐፍ የሌለ ልዩ አምልኮና ዝክር የምታደርግ ሴት እንደነበረች ልብ ይሏል::

ስለ ሚካኤል በዓል አከባበር ጸሐፊዎቹ ሲያብራሩ « በምድር ረኃብ በነበረ ጊዜ እግዚእ ኀረያ የሚካኤልን በዓል ማክበር አልቻልሁም ብላ ስታለቅስ ባሏ ጸጋ ዘአብ ወደ ቤተ መቅደስ ሄዶ ዝክሩ ሊታጎልብኝ ነው ብሎ በመንበሩ ሥር ወድቆ ጸለየ፡ እግዚእ ኀረያ የ1 ዓመት ከ3 ወር ልጇን ( ተክለ ሃይማኖትን

) ታቅፋ እያለች ሕፃኑ ወደ ቤት አስገቢኝ እንደሚል ጠቅሶ እናቱን ወደ ቤት አስገባት ሕፃኑም በቤት ውስጥ በነበረው ወጪት እጁን ቢጭነው ዱቄቱ በተአምራት ሞልቶ ፈሰሰ የቤቱ ዕቃ በሙሉ በዱቄት ተሞላ እናቱም « ይህ ሕፃን እንደፈጣሪው ሁሉ ይቻለዋል » ብላ አሰበች ይላል ::(ምዕ18÷1-18)

የዚህ ገድል ጸሐፊዎች ከዚቅ ደራስያን ትንሽ ብልጥነትን የተላበሱ ይመስላሉ የሚካኤልን በዓል እንዲያከብሩ በመቅደስ ይመለክ የነበረው እግዚአብሔር እንደተባበራቸው ተርከዋል:: ( ምዕ 18 ÷ 25 ) ከዚህ የተነሣ መጋቢት 12 ቀን በሚካኤል ስም ታላቅ በዓል አደረጉ ብለዋል::

ከዚህ የተነሣ ተደረገላቸው በተባለው ተአምራት ሰዎች ሁሉ ( በድግሱ የታደሙት ) ተደነቁ እንዲህም አሉ « በሃገራችን እህል የለም በረኃብ ዘመን ይህን ያህል ምግብ ከየት አገኙ? እኛም እኮ የሚካኤልን ዝክር ብንዘክር እንዲህ ባገኘን ነበር » ተባባሉ :: ይህን የጸሐፊዎቹን አካሄድ በሰከነ ኅሊና ስንቃኘው አላማቸው ለእግዚአብሔር ክብር ሳይሆን እነሱ ለሚሰይሟቸው ቁጥረ ብዙ መናፍስት ክብርና ውዳሴ ለማስገኘት እንደሆነ ግልጽ መረጃ ይሆነናል:: ( ምዕ 18 ÷ 26 )

እንደ ታዳሚዎቹ ሃሳብና እንደ ገድሉ ፀሐፊዎች ዓላማ በረከትን ሊሰጥ የሚቻለው በተለያየ መናፍስት ስምና ቀን ድግስ ደግሶ የተደገሰለትን ሰው ሆነ መንፈስ ሲዘምሩለት ስሙን ሲያወድሱት እንደሆነ ነው :: መጽሐፍ ቅዱስ ግን « <u>ወውእቱ ይሁብ ዘርዐ ለዘራዒ ወእክለ ለሲሳይ</u> » ትርጉም « <u>ለዘሪ ዘርን ለሚበላ እንጀራን በብዙ የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው</u> » በማለት ይናገራል ( 2ኛ ቆሮ 9 ÷ 9 - 10 ) ጌታችንም በሥጋ በምድር በነበረበት ጊዜ እንደ ገድሉ ጸሐፊዎች በረከትን የሚሰጥ መንፈስ ወይም እንወደዋለን የሚሉት ሰው እንዳልሆነ ሲያስተምራቸው::: « <u>አኮ ሙሴ ዘወሀበክሙ ውእተ ኅብስተ እምሰማይ አላ አቡየ</u> » ትርጉም « <u>እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቱ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራን የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም</u> » አለ :: ( ዮሐ 6 ÷ 33 ) ሙሴ በምድረ በዳ እንጀራን ከሚሰጥ ከእግዚአብሔር ታዝዞ አቅርቦላቸው ነበረና እንጀራን ሁሌ በሙሴ እጅ እንደሆነ ያስቡ ነበር:: ያም ቢሆን ሙሴን እንዳያመልኩት እግዚአብሔር ሰወረው ይላሉ እውነተኞቹ መምህራን :: ምክንያም እግዚአብሔር ክብሩን ለማንም ይሰጥ ዘንድ አይፈቅድምና

## የዳዊትን መንግሥት በዶሮ ጭንቅላት

ቤተክህነትና ቤተ መንግሥት በእግዚአብሔር ዓላማና ዕቅድ መሠረት ክብሩን ሊገልጥባቸው ሕዝብን ሊያስተዳድርባቸው የመሠረታቸው መዋቅሮቹ ናቸው:: ሆኖም ሰይጣን በዕቅዱ መሠረት በከንቱ ሰው ኃሳብ በመጠቀም ሁል ጊዜ የእግዚአብሐርን ሥራ መቃረን ከባሕርዩ የመነጨ ፍላጎቱ በመሆኑ እነዚህን ክፍሎች ቢቻለው ( አይሆንም እንጂ) መውረስ ካልተቻለው መበረዝ የዕለት ተዕለት በትጋት የሚሠራው ተግባር ነው ::

በመሆኑም ከጥንት ጀምሮ በቤተ-መንግሥትና በቤተ ክህነት ዙሪያ መረቦቹን በመጣል በርካታ የእግዚአብሔርን ሰዎች ሳይቀር እንደጣለ ታሪካቸውን እንዳበላሸ የነገሥታትን መጽሐፍ ማንበቡ በቂ ይሆናል:: ወደ ሀገራችንም ስንገባ ከዚህ ያልተናነሰ ( እንዲያውም ቢበልጥ ) መናፍስታዊ አሠራር በሁለቱ መዋቅሮች ከፍተኛ ሥፍራ አግኝቶ ለማይቆጠሩ ዘመናት ሲሠራ ቆይቷል::

በሀገራችን ነግሠው የነበሩ በርካታ ነገሥታት ከንግሥናቸው ሥርዓት ጀምሮ እስከ ዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴያቸው ድረስ በብዙ የመናፍስት አሠራር ይጠቀሙ እንደነበር አብረዋቸው የነበሩ ፡ ሠራተኞቻቸው ጠባቂዎቻቸውና የቅርብ ጓደኞቻቸው እንዲሁም በመናፍስቱ አሠራር ይረዷቸው የነበሩት መናፍስት ጠሪዎቻቸው ዛሬ እውነተኛ ክርስቲያኖች ሆነው የሚናዘዙት ገሃድ ነው::

በተለይ ይህን ግብር በመፈጸም ረገድ ባለሟሎች የነበሩት አንዳንዶች በልዩ ልዩ ምክንያት ሥልጣነ ክህነታቸውን አፍርሰው የታገዱ ፣ አንዳንዶችም በቅኔ በዜማና በየአቋቋም ቤቱ ለትምህርት
እየተባለ ይዞሩ የነበሩት ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው « ጥበብ አብነት ወ.ዘ.ተ » እየተባለ ተነግሯቸው በተዋረሱት ትምህርት የመናፍስት ሠራተኞች በመሆኑና እነዚህም ሰዎች በቤተ መቅደሱ ዙሪያ ነዋሪዎች በመሆናቸው ያለ ከልካይ ብሔራዊ እዳችን እንዲሆን አ ድርጎታል::

ብዙዎች እንደሚሉት ይህን የርኩስ መንፈስ አሠራር ሃይማኖታዊ ድጋፍና እግዚአብሔርም የሚተባበርበት ለማድረግ ፈጠራዎችን በልዩ ልዩ ጽሑፋቸው አስገብተዋል:: ለምሳሌም በሥነ ጽሑፍ ታሪክ እነዚሁ ጀሌዎቻቸው የሚያደንቋቸው ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የተባሉ ሰው ( በእነርሱ ቅዱስ ) «

ከብቃታቸው የተነሣ ሰይጣንን ጠርተው ድንጋይ አሸከመው በማምጣት ለቤተ-ክርስቲያን ለደወልነት እንዲያገለግል አድርገዋል




አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሰይጣንን አሸክሞ ያመጣው የድንጋይ ደወል

ንጉሥ ሰሎሞንም ሰይጣንን በቀለበቱ ላይ ባለው ድግምት እየተጠቀመ እንደ ቤት ሠራተኛው ሰይጣንን ያሠራው ነበር በማለት መናፍስት ጠርቶ ማናገር ክርስቲያናዊና እግዚአብሔርም የሚደግፈው እንደሆነ ለማሳመን ጥረዋል:: እንዲያውም ተክለ ሃይማኖት የተባሉት ሰው ሰይጣንን ወንጌል ሰብከው ገርዘው ስሙን ክርስቶስ ኀረዮ በማለት ሰይመውና አመንኩሰው ባለዘመኑ ሁሉ መነኮሣቱን በቅንነት አገልግሎ ሲሞት መንግሥተ ሰማይ እንዳስገቡት በገድሉ ላይ ሳያፍሩ በገሃድ አስፍረውታል (ገድ ተክ/ሃ ምዕ 48 )::

በተአምረ ማርያም መጽሐፍም በገዳም በማርያም መልካም ፈቃድ ሰይጣንን በመጥራት ገርተውት ዳቤ እየጋገረ እንጨት እየሰበረ መነኮሳቱን ይረዳ ነበር ተብሎም ተጽፏል::

ይህ ሁሉ እነዚህ ውኋቸውና አዳራቸው ሳይቀር ቤተመቅደስ የሆነውና በቤተ መቅደሱ የጩኸት አገልግሎት ሠራተኞች በሆኑት ነፃ የሚያወጣው የእግዚአብሔር ንጹሕ ቃልና መንፈሱ የሌላቸው ሰዎች መናፍስትን መጥራትና መገናኘት የኃጢአት ያህል ሳያሰቅቃቸው እግዚአብሔርን እንደበደሉም ሳይሰማቸው ሲለማመዱትና የዋሁን ሕዝብ አሳልፈው ሲሰጡት ኖረዋል ::

በዚህ የመናፍስት ሥራ ነገሥታትና መኳንንት ተገዥ እንዲሆኑ ተደርጎ ሥልጣን ለመያዝ ሆነ ሥልጣን ለማርዘም ጥበበኞች ተብለው በሚጠሩት ሰዎች ምሪት በመወሰዳቸው ቤተክህነቱ ብቻ ሳይሆን ቤተ መንግሥታችንም ሳይቀር በእነዚህ ሰዎች እጅ ወድቆ ይገኛል።

ይህንንም እንደ ቅዱስ ተግባር አድርገው በማጻፍ መጻሕፍቱንም ሕዝቡ እንዲሳለማቸው እንዲጸልይባቸውና እንዲማጸንባቸው ተደርጎ እነሆ ሥር ሰደላቸው የዛሬን መከራ ተሸክመን እንገኛለን። በዚህ ገድለ ተክለ ሃይማኖት እየተባለ በሚጠራው መጽሐፍም ይህንኑ እውነት የሚያረጋግጥልንን መረጃ እናገኛለን።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ከቁጥር ሠላሳ ሁለት ላይ እውነተኛውና በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን መጸነስ ሲያበሥራት «<u>እነሆ ትጸንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ እርሱም ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል</u> » አላት ። ይህም ለንጉሥ ዳዊት በትንቢት « ከቤትህ ንጉሥ አይጠፋም » ያለው ምሥጢር እንደሆነ ያመለክተናል። በእግዚአብሔርም የዘላለም እቅድ የዳዊትን መንግሥት ለዘላለም የያዘ አንድ ብቻ እንዳለ መጽሐፍ ይመሠክራል ። እርሱም በሥጋ የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ይህም መንግሥት ለማንም የማይሰጥ መንግሥት እንደሆነ ነቢዩ ዳንኤል አስቀድሞ ተናግሯል።ዳን 2 44 )

በገድሉ ምዕራፍ 25÷ 4— ምዕ 27÷ 4 ድረስ ባለው ታሪክ ግን ጸሐፊዎቹ በተለማመዱት መናፍስታዊ አሠራር የሀገራችንን ቤተ መንግሥት አመሠራረት እንዲህ ይገልጡታል ።« <u>አንድ ዶሮ የእኔን ራስ የበላ ይነግሣል፣ የዳዊትን መንግሥት ይወርሳል፣ በዓለም ነግሦ ይኖራል መንግሥቱ ወደ ሌላ አይሄድም እያለ ሦስት ወር ያህል እንዲህ እያለ ጮኸ</u> » ይላል ። በዚህ መሠረት ዶሮው እንዳለውና ጸሐፊዎቹም እንደሚስማሙበት የዶሮውን ራስ የበላ :-

1ኛ. ንግሥና ያገኛል ፣

2ኛ. ንግሥናውም የዳዊት መንግሥት እያለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠራውን ነው

3ኛ. ንግሥናውም በዓለም ሁሉ ነው።

4ኛ. መንግሥቱም ወደ ሌላ አይተላለፍበትም ( አይነጠቅም )

ይህን ህልም ያየና የሰማ የተባለው ንጉሠ እልመክኑን /ይትባረክ/ በወቅቱ የሃይማኖቱን ክፍል ይዘውት ነበር ለተባሉት ለተክለ ሃይማኖት ነገራቸው። ተክለ ሃይማኖትም ፦ « ያ ዶሮ የኔን ራስ የበላ መንግሥት ከወገኑ አይወጣም እስከ ልጅ ልጅ ይነግሣል ብሎ እንደነገረህ ፈጥነህ ዶሮውን ይዘህ አርደህ ብላው አለው » ይላል ገድሉ። ( ምዕ 25÷ 13 )

ልብ እንበል መንፈሳዊ አባት እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት ያውም በአዲስ ኪዳን ነገሮች ሁሉ ግልጥና ቀጥተኛ በሆኑበት ዘመን እንደ አስማተኞችና እንደጠንቋዮች የመሥዋዕት ሥርዓት የዶሮን ራስ በመብላት መንገሥ ይቻላል ብሎ መምከሩ የነገሩን ጥልቅና ምሥጢራዊ አሠራር የሚያሳይ ነው። የሚገርመው ተክለ ሃይማኖት ይህን በዶሮ ራስ ንግሥና ጥያቄ ለመመለስ የአንድ ሰዓት የጥሞና ( የጸሎት ይሁን የድግምት ) ጊዜ ከወሰደ በኋላ ነው የሚለው መጽሐፍ ነው።

= ማንም ከኢየሱስ በስተቀር የዳዊትን ዙፋን (መንግሥት ) የሚወርስ ወይም የሚቀበል ንጉሥ የለም

= መንግሥት ሆነ ሥልጣን በእግዚአብሔር ምርጫና ጸጋ እንጂ በዶሮ ራስ መሥዋዕት አይደለም ይህ የአሕዛብ ልማድና ወግ ነው፡

ታሪኩ ይቀጥልና ንጉሡ ተክለ ሃይማኖት እንዳዘዘው ዶሮውን አሳርዶ ሠራተኛው እንድትሠራለት አድርጎ ለመብላት ወሰነ። ሆኖም ሠራተኛዋ የዶሮውን ራስ አውጥታ ጥላ የቀረውን ሥጋ አቀረበችለት። ንጉሡም የዶሮውን ራስ ባጣው ጊዜ እጅግ አዝኖ ወደ ተክለ ሃይማኖት እንደሄደ ይተርካል ።

ሠራተኛዋ የጣለችውን የደሮ ራስ አንድ ሕፃን (ይኩኖ አምላክ) ( በሕፃንነቱ ከሸዋ ክፍለ ሀገር በጦርነት ተማርኮ የሄደ ልጅ ነው በዚያም ሆኖ ለንጉሥ ፈረሶች ሣር እያጨደ ይመግብ ነበር )አግኝቶት በበላው ጊዜ ከሁሉ በላይ እስኪሆን ድረስ ኃይል ተሰማው፡ ፊቱም እንደፀሐይ ብሩህ ሆነ ግርማውም የንጉሡን ባሮች ሁሉ አስፈራቸው ። ( 26 ÷ 1-5 ) የሚገርመው የዶሮውን ራስ የበላው ሕፃን « ሀብተ እግዚአብሔር አደረበት » ብለውታል።

በቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው ተክለ ሃይማኖት የሚባለው ሰው መደቡ ላስታ የነበረውን የዛጉዬን መንግሥት ለማስገልበጥ በተደረገው ሤራ ማለትም ይትባረክን አስገልብጠው ይኩኖ አምላክ የተባለውን ሰው ለማንገሥ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ዘዴ ተጠቅመው እንዳስፈጸሙ የሚነገርላቸው ሰው ናቸው።

# የይኩኖ አምላክ ንግሥና (በዶሮ)

ይህ ከሆነ በኋላ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መልአክ ወደ ተክለ ሃይማኖት መጥቶ እንዲህ አለው ይላል ገድሉ « ለዳዊት ልጅ ለይኩኖ አምላክ የጌታውን መንግሥት መልሸለታለሁ » እርሱም ( ተክለ ሃይማኖት ) እንዲያነግሠው እግዚአብሔር እንዳዘዘው ነገረው። ተክለ ሃይማኖትም እንዲያነግሠው በታዘዘው መሠረት :- ስሂን ፣ ሚዓ ቀንሞስ ፣ ቀናንሞስ፣ ጽስጥቂስ ፣ ዕንጉታት ማየ ከርካዕ ፣ ኮል ፣ የወይን ፍሬ ወ.ዘ.ተ እነዚህን በአንድ ጽዋ በማድረግ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ዕጣን እያጨሰ ታቦቱን 3 ሱባኤ ( 21 ቀን ) እንዲያጥን ከዚያም በኋላ ከመዝሙረ ዳዊት ፣ የነቢያትን ጸሎት ማለትም -

1. ጸሎተ ሐና
2. ጸሎተ ማርያም
3. ጸሎተ ዘካርያስ
4. መኃልየ መኃልይ
5. ውዳሴ ማርያም
6. አንቀጸ ብርሃን በደገምህ ጊዜ በጽዋው ያለው ሽቶ ፈልቶ ይፈላል : ያን ጊዜ ይኩኖ አምላክን ቅባው :: ብሏል በማለት እግዚአብሔርን በዶሮ ራስ መብላት የዳዊትን መንግሥት መውረስ ያስችላል የሚለውን የመናፍስት ጠሪዎች ትምህርት ተባባሪ አድርገው ጽፈውታል:: ( 27 ÷ 6 - 13 )

ልብ የሚባሉ ነገሮች :-

1ኛ. ይሁን ብንል እንኳ የተገለጡት ቅባቶች በየትኛው የመጽሐፍ ቅ ዱስ ክፍል ለዚህ ሥራ እንደሚውሉ ሊገኙ ይችላሉ ?

2ኛ. በአዲስ ኪዳን የታቦት ሥርዓት በተሻረበትና በምትኩም ሌላ ኪዳን በተገባበት ዘመን እግዚአብሔር ታቦቱን እየዞራችሁ ዕጣን እያጠናችሁ አምልኩኝ ያለበት ክፍል ሊገኝ ይችላል ወይ?

3ኛ. ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና ጌታችን በሥጋ ሰብእ ተገልጦ የነበረውን የጥል ግድግዳ ካፈረሰ በኋላ ስለ ጸሎት ሲያስተምር « እስካሁን በስሜ አልጸለያችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን በስሜ ጸልዩ » (ዮሐ16÷24) እንዲሁም በስሜ የምትለምኑትን አባቴ ይሰጣችኋል፣እኔም አደርገዋለሁ (ዮሐ14÷14) እያለ ጸሐፊዎቹ በዶሮው ራስ እንዲነግሥ ያዘጋጁትን ሰው

እግዚአብሔር ከላይ የተዘረዘሩትን የጸሎት አይነቶች ድገም ብሎታል ማለት ወንጀል አይደለም ወይ ? በአባትና በልጅ ( በአብና በወልድ ) መካከል ያለችውን አሐቲ ፈቃድ በመጣስ በፈቃድም እንደማይስማሙ አድርገው አቅርበውታል።

ሌላውና የደራሲዎቹን የተደበቀ ሤራ የሚያጋልጠው እግዚአብሔር ለተክለ ሃይማኖት « ይህን ቅብዓ መንግሥት ( የመንግሥትነት ቅብዓት ) ከእርሱ በኋላ የሚነግሡ ነገሥታት የሚቀቡት አይደለም « ዘርዓ ያዕቆብ » ብቻ ነው እንጂ አለው የሚለው ኃሳባቸው ነው ። ( 27÷14 )

በርግጥ መናፍስት የእነርሱ የሆኑትን ስለሚያውቁ በትክክል ለዚህ ሥራቸው ዋና ተዋናይና ሠራተኛ ለሚሆነው ለዘርዓ ያዕቆብ መመደባቸው አያስደንቅም። አንባቢ የነገሩን መናፍስታዊ አሠራር
በትክክል ይረዳው ዘንድ ቅባቱን እንዲወርስ የታጨውን ሰው ታሪክ በጥቂቱም ቢሆን ለማሳወቅ እንወዳለን ።

# ዘርዓ ያዕቆብ ማን ነው ?

ከአፄ ዳዊትና ከእቴጌ እግዚእ ክብራ ተወለደ ተብሎ የሚነገርለት ዘርዓ ያዕቆብ አባ ፊልጶስ ከሚባል ሰው ዘንድ በመሄድ እንደተማረና የመምህሩን ትምህርትና ባሕርይ ወርሶ ያደገ እንደነበር ታሪኩን ያጠኑ ጸሐፍት ይገልጣሉ።

ከመምህሩ ይዞት ያደገውን የሁለት ሰንበታት ( ቅዳሜና እሑድ ) አክብሮትና ሌላም ትምህርት የአባቱን መንግሥት ከተረከበ በኋላ በጊዜው የነበሩትን ጳጳስ አባ በርተሎሜዎስን በመጋፋትና ጫና በመፍጠር የሁለት ሰንበታት አክብሮትን ይፋ አደረገው።

አንዳንድ ጸሐፊዎች በድንግል ማርያም ስም ሸፍነው በሚጠሯት « የሰማይ ንግሥት » ልዩ ፍቅር ነበረው የሚባለው ዘርዓ ያዕቆብ ከንግሥናው ባሻገር የምንኩስናን ሥራ እሠራለሁ ብሎ ያስብ ስለነበር ለመንፈሳዊ አገልግሎት እንዲውሉ በሚል ሽፋን በርካታ መጻሕፍትን ይጽፍና ያጽፍ እንደነበር ዛሬም በደጋፊዎቹ የሚወደስለት የሚነገርለት ታሪኩ ነው።

ለማርያምና ለመስቀል ስግደት እንዲሁም ሁለት ሰንበታትና ተጨማሪ በዓላትን ማክበር ይገባል የሚለውን ትምህርት አራማጅ የነበረው ዘርዓ ያዕቆብ

ይህን ኃሳቡን በእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል የተቃወሙትን ሁሉ በብዙ መከራና ስቃይ ይገድል እንደነበር ወዳጆቹ ነን የሚሉት እንኳ ጽፈውለታል።

በተለይ በ1932 ዓ.ም ( አንዳንድ የታሪክ መጻሕፍት ከ1426 - 1460 እንዲሁም ሌሎች ደግሞ ከ1434 - 1468 ብለው ጽፈውታል ሆኖም የታሪካቸው ይዘት በሁሉም በኩል አንድ ዓይነት ነው።) በደብረ ምጥማቅ በጠራው ጉባኤ ከንቱ ትምህርቱን በማጽደቅ ብሔራዊ ዕዳችን እንዲሆን ከውግዘት ጋር አስተላለፈ። ( የአማርኛ መዝገበ ቃላት በስርግው ሐብለ ሥላሴ)

ለ34 ዓመት እንደገዛ የሚነገርለት ዘርዓ ያዕቆብ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ሄዶ እንደነበር ይታወቃል። ( አጤ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት በተክለ ጻድቅ መኩሪያ ) ይህን ታሪክ አንዳንድ ሲቃውንት በሃገራችን በዘመነ ዘርዓ ያዕቆብ እንደ አሸን የፈሉትን የስዕላትና የቅርጻቅርጽ አምልኮ ንጉሡ ይዟቸው የመጣው ከዚያ ነው በማለት ይናገራሉ።

እንደመረጃ የሚያቀርቡትም በሩቅ ምሥራቅ ያሉ ኢአማንያን የሚያመልኳትና የሚያጥኑላት « የሰማይ ንግሥት » የምትባለዋ ሴት ምሥል ዛሬ በሃገራችን በቤታችን እናት ስም አስመስለው ድንግል ማርያም እያሉ የሚሰግዱላትን የሚያጥኑላትን ምስል በመልክ በቅርጽ ተመሳስለው መገኘትን ነው። የሚገርመው የእኛዎችም ሰዎች ይህችን ስዕል « ንግሥተ ሰማይ ወምድር » በማለት መጥራታቸው ነው ።

እንግዲህ በተክለ ሃይማኖት ገድል እንደተገለጠው በዶሮ ራስ ተገኘ የተባለውን ንግሥናና የንግሥና ቅባት ሊወርስ የሚችለው ይህ ዘርዓ ያዕቆብ ነው መባሉ « ዘር እንደወገኑ ያፍራ የሚለውን የፍጥረት ሕግ እንድናስብ ያደርገናል።

በ1278 ነበሩ የተባሉት ተክለሃይማኖት ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ ለሚነሣው ሰው ያወረሱት የመንግሥት ቅባትና ንግሥና ከክርስትና ውጪ መሆኑን ተዋራሹ ዘርዓ ያዕቆብ በታሪኩ አስረግጦታል።

# ወደ መንግሥተ ሰማያት የይለፍ ፈቃድ

የገድሉ ጸሐፊዎች ዋና ዓላማቸው ሕዝቡ በክርስቶስ በመድኃኒታችን አምኖ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ሳይሆን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የሰይጣንን ፈቃድ ለማሳካት የተነሡ መሆናቸውን ጽሑፋቸው ያጋልጣቸዋል::

« መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ሚካኤልን በቀኙ፣ገብርኤልን በግራው አድርጎ እናቱ ማርያምን 12ቱ ሐዋርያትን ከእርሱ ጋር ይዞ ብዙዎች የሰማይ ሠራዊትን አስከትሎ ወደ እርሱ ( ተክለ ሃይማኖት ) መጣ : እንዲህም አለው:: « በዓልህን የሚያከብር በእንጀራም ቢሆን በዕጣንም ቢሆን በመሥዋዕትም ቢሆን እስከ ጥሩ ውኃ ድረስ ስምህን የሚያስጠራ ሁሉ ባንተ ስም እንግዳ ቢቀበል በግልጽ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይለፍ ... ስምህ በተጠራበት በገዳምም ቢሆን በዓለምም ቢሆን እስከ ዘላለም ይቅርታና ቸርነት ከዚያ ይኑር በእውነት ያለ ሐሰት ... » ይላል ( ምዕ 39÷ 2-6 )

እንደ ጸሐፊዎቹ ኃሳብ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት በተክለ ሃይማኖት ስም እንግዳ መቀበልና እንጀራና ዕጣን መስጠት ይገባል ብሎ አስተምሯል ማለት ነው:: ሆኖም ለአነዋወሩ ነቀፋ ለንግግሩ ሐሰት ለትምህርቱ ስሕተት የማይገኝበት በእኛ ሥጋ ለመዳናችን ሥራ ሲል በሥጋ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ በሰውነቱም የሰው ልጅ የተባለው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎ አስተምሯል:: ማለት በእርሱ ላይ ስድብ እንደመናገር ይቆጠራል:: በየትኛውም ትምህርቱ ጻድቅ እየተባሉ በተጠሩ ሰዎችና መላእክት ስም በሚደረግ ስጦታና በዓል ማክበር መንግሥተ ሰማያት ይገኛል ብሎ አላስተማረም::

እንዲያውም ጌታችን ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት በዚህ ምድር በነበረበት ጊዜ ሲያስተምር « መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ » ብሎ ( ማቴ 4 ÷17 ) መግቢያ በሩ እኔ ነኝ በእኔ የማይገባ እርሱ ሌባ ነው አለ እንጂ በተክለ ሃይማኖትና ቅዱሳን እያልን በምንጠራቸው ሰዎች ሆነ በመላእክት ይቻላል አላለም::

ከተከታዮቹ አንዱ ፊልጶስ ወደ አብ ለመሄድ መንገዱን እንዲያሳየው በጠየቀው ጊዜ መድኃኒታችን ሲመልስ « እኔ መንገድ ነኝ ... በእኔ ካልሆነ በስተቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም » በማለት ተናግሯል።(ዮሐ14÷6 )

ምሥጋና ገንዘቡ የሆነ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይክበር ይመስገንና ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስተምር በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለወንጌል አገልግሎት ሲሄዱ ወንጌልን ሲያስተምሩ ስለሚቀበሏቸው ሰዎች የተነገረ በስሜ እናንተን የተቀበለ እኔን ይቀበላል በስሜ ጥሩ ውኃ ያጠጣ ዋጋው አይጠፋበትም አለ እንጂ (ይህም ቢሆን ደቀመዛሙርቱ በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለወንጌል አገልግሎትም ሲዞሩ ለሚቀበሏቸው ነው ) በሰዎች ስም እንግዳ የተቀበለ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይለፍ ብሎ አልተናገረም። እንዲያውም « የምታደርጉትን ሁሉ በስሜ አድርጉት » ተብለን ሳለ « በስምህ ( በተክለ ሃይማኖት) ስም ብለው በመተካት የጌታን ስም ለማስረሳት ብዙ ጥረዋልና ትምህርታቸው አስከዛሬ ፀረ ወንጌል የሆነው ለዚህ ነው።

ጸሐፊ ገድለተክለ ሃይማኖት ግን ጌታችን የተክለ ሃይማኖትን በዓል የሚያከብርና በስሙ እንግዳ የሚቀበል ያለምንም ችግር ወደ መንግሥተ ሰማያት ይለፍ የሚለውን ትዕዛዝ አስፍሯል። ይህም ምን ያህል የወንጌሉ ተጻራሪ እንደሆኑ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡

# 10 ትውልድ
# በዝክረ ተክለ ሃይማኖት

«ኵሉ ሰብእ ዘይገብር ተዝካረከ አነ እምሕሮ እስከ ፲ቱ ትውልድ

ትርጉም :

« መታሰቢያህን (ዝክርህን) ለሚያደርግ ስምህን ለሚጠራ ሰው እኔ እስከ 10 ትውልድ እምረዋለሁ»(ገደለ ተክለ ሃይማኖት ምዕራፍ )

<u>ለመሆኑ ዝክር ምንድን ነው ?</u> :-

ዝክር ( ተዝካር) ማለት መታሰቢያ ማለት ሲሆን የአንድ ነገር ዕለታዊ ፣ወርኃዊ፣ዓመታዊ ወ.ዘ.ተ እየተባለ ለክንውኑ የሚደረግለት የትውስታ ቀን ነው። በተለይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በርካታ ዝክር ወይም ተዝካር

የሚደረግባቸው ምክንያቶች ቢኖሩም ደምቆና ልቆ የሚታየው ግን ከሚበላው ከሚጠጣው ድግሥ ጋር ተቆራኝቶ የሚገኘው የሙታን ዕለታዊ ወርኃዊና ዓመታዊ የሙት ቀን መታሰቢያ ነው።

ከ7ኛው ቀን እስከ 7ተኛው ዓመት ድረስ በተመደቡለት ቀናት በሚደረግ የእህል ውኃ ዝግጅት ለቀሳውስቱና ለዘመድ አዝማድ ቢቀርብ የሟች ኃጢአት ጥርግርግ ብሎ ተወግዶለት ከሲኦል ወደ ገነት የቦታ ለውጥ አድርጎ እንደሚጸድቅ ለዘመናት ሲሰበክን የኖረ ነው። ምንም እንኳ የሃይማኖት እውቀት ሳይሆን ጊዜው ያመጣው የኑሮ ውድነት ከትከሻችን ላይ ወርውረን እንድንጥለው ግድ ያለን ይህን የሙታን ተዝካር ማውጣት ጉዳይ ለአንዳንዶች ባይዋጥም ዛሬ ያጸድቃል የተባለለትን ሥልጣን አጥቶ የሃይማኖት መሪዎቻችን ተቀምጠው ድጎነቱ የጠበሰው ምዕመን በዕድርና በማኀበር ተቀምጦ ተዝካር ማውጣት ብቻ ሳይሆን ለተዝካር ተብሎ የተደገሰ የበላ ሳይቀር ከማኀበራዊ ኑሮ ሁሉ እንዲከለከል እየተወሰነ በመምጣቱ በሚቀጥሉት ዓመት ከዚህ እሥር ትውልዱ እንደሚፈታ ፍንጭ ታይቷል።

ሌላው ዝክር ደግሞ ጻድቅ ነበር የተባለው ( መልአክ ሆነ ሰው ) ተጋደለበት፣ ድል አደረገበት፣ ታሰረበት፣ ተፈጨበት፣ ነፍሱ ከሥጋው ተለየችበት፣ አረገበት፣ ቃል ኪዳን የተገባለት ቀን ተብሎ በነመምሬ አታላይ የተቀመሩትን ቀናት አስቦ ከገንቦ ጠላ እስከ በርሜል ጠጅ ከዶሮ ሥጋ እስከ ሠንጋ በሬ ድረስ ዝግጅት ተደርጎ የሚከበርበት የመታሰቢያ ድግሥ ነው።

ይህም ለደጋሹ የቅዱሱ ሰው ወይም መልአክ ቡራኬ ( በረከት) እንደሚደርሰው በዚህም ምክንያት ጻድቁ ሰው ወይም መላእክት እነ የኔታ ሥራው ብዙ እንደሚሉት ዝክራቸውን ያደረገውን መታሰቢያቸውን ያከበረውን ሰው ከአንድ ከራሱ እስከ አንድ አውራጃ ሕዝብ ድረስ ያለ ዘመድ አዝማድ የሠሩት ኃጢአት ሁሉ ታጥቦ መንግሥተ ሰማያት ሰተት ብለው እንዲገቡ የመግቢያ ቪዛ የሚቀበልበት እንደሆነ የሚሰበክን ዝክር ነው።

ሌላውና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ዝክር ( መታሰቢያ ) ሌትና ቀን ሊዘከር ለሚገባው አምላክ የሚሆን ከመብልና ከመጠጥ ጋር የነበረውን ሥርዓት ሰብሮ በመንፈስ የሚደረግ መንፈሳዊ ዝክረ በዓል ነው።

ይህም ቢሆን ዝክሩን ( መታሰቢያ በዓሉን) ለሚያከብሩ የገነት በር መግቢያ መክፈቻ ሳይሆን በከበረ ልጁ ሥራ መንግሥተ ሰማያት ያስገባንና የዘላለም

ሕይወት በጸጋው ለሰጠን አምላክ ያለንን ፍቅር ለመግለጥ « ቀናትን ሁሉ ለእርሱ ለመግዛት» የምናሳየው ፍቅር ብቻ እንደሆነ የታወቀ ነው።

እነ መንገደ ብዙ ግን ቁጥሩ የማይታወቅ የመላእክት ነገድ ፣ መቼና ከየት አገር እንደመጡ እንኳ በቂ እውቀትና መረጃ ላይቀርብባቸው እንዲሁም ምን እንደሰሩ በውል ላልተረጋገጠ ባለታሪክ ሰዎች ስም መታሰቢያ ( ዝክር) ያደረገ ሁሉ ያለ ክርስቶስ ሞት በአጭሩ በአቋራጭ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገባ ሌትና ቀን የዋሁን ሕዝብ ይግቱታል።

በሐረር ከተማ ስሙ የታወቀ ምግብ ቤት ባለቤት የነበሩ አንዲት ሴት ከተመጋቢዎቻቸው ፊት የተራረፈውን እያጠራቀሙ በአካባቢው ለሚገኙ ችግረኞች እየሰጡ ያበሉ ነበር። በአካባቢው ከሚገኙት አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች ስመ ጥር ከነበሩት በአንዱ የሚገኙት የንሥሐ አባታቸው የነበሩት አባት እንደ ንስሐ አባትነታቸው ቃለ እግዚአብሔርን አስተምረው በክርስቶስ የሚገኘውን ጽድቅና ቅድስና እንዲያገኙ ከማድረግ ይልቅ « አንቺ እኮ ምንም አያስፈልግሽም እንዳንቺ ዛሬ ጊዜ ማን ያደርጋል ይህ ብቻ መንግሥተ ሰማያት ያስገባሻል » በማለት ያበረታቷቸው ነበር። በርግጥ ድሆችን ማብላት መልካም ግብር ቢሆንም የሟች ተዝካር መደገስ ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ የመግቢያ ካርድ ሊሆን እንደማይችል ግን እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን።

እንደ ካህኑ አባባል በዚህ ዘመን ( ሰው ክፉ በሆነበት ትግር በበዛበት ማለታቸው ነው) እንዳንቺ ማን ያደርጋል ማለታቸው ሴትዮዋ የተሻሉ ሰው ለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር በዘመናቱ ባሕርይ ማለትን ሰው ሲከፋ የተሻለ ክፉ እየመረጠ ሰው ደግ ሲሆን የተሻለ ደግ እየለየ የሚያጸድቅ ሳይሆን የማይሻሻል የማይለወጥ የጽድቅ መንገዱ በክርስቶስ ሞት ማመን ብቻ እንደሆነ የታወቀ ነው። « እስመ ከመዝ አፍቀሮ እግዚአብሔር ለዓለም እስከ ወልዶ ዋሕደ ወሀበ ቤዛ ከመ ኩሉ ዘየአምን ቦቱ ኢይትሐጎል አላ ይረከብ ሕይወተ ዘለዓለም » እንዳለ ወንጌላዊው ዮሐንስ ( ዮሐ 3 ፥ 16 )

ዝክርን ( አርባ ሰማንያን ) በተመለከተ በአንዲት የዋህ እናት ላይ የተፈጸመውን ወንጀል እንመልከት« ሴትዮዋ እኅታቸው ትሞታለች ከድኅነታቸው የተነሳ ከ7ኛው ቀን ጀምሮ እስከ 1 ዓመት ድረስ ምንም ዝክር ሳያደርጉ ቆይተው ነበር። ከ1 ዓመት በኋላ ሟች እኅታቸው በተደጋጋሚ በሕልማቸው እየመጣች ሲቸገሩ ነገሩን ለነፍስ አባታቸው ያስረዳሉ።

የኔታም « ለመሆኑ ተዝካሩን አውጥተሽ ነበረ ወይ ? » አሉ:: ወይዘሮዋም የለም በማለት መለሱ:: አየሽ አሉ የኔታ :- እንዲህ የሆንሽው የሟቿ ነፍስ ከዚህ አውጭኝ እንደማለት ከሲኦል ሆና እየጠራችሽ ነው አሉ :: የእህታቸው ነፍስ በሲኦል እንዳለች የተረዱት እናትም ፈጠን በማለት እና ምን ላድርግ አባቴ ? በማለት ካህኑን ጠየቁ : የኔታም አየሽ ወለተ ማርያም አሉ በንስሐ ስማቸው እየጠሩ ::

እኛ ሰዎች ስንባል አይሞላልንም የፈጣሪንም ሕግ አንጠብቅም ስንሞት እንደሚታወቀው በሥራችን ስለሚፈረድብን ያው ሲኦል ነው የምንገባው: ሆኖም ቸሩ አምላካችን የሚያድንበት መንገዱ ብዙ ነውና ቋሚ ዘመድ ስለሟች ዝክር አድርጎ ቢለምኑት ለዚያች ሟች ነፍስ ምህረት እንደሚያደርግ ቃል ኪዳን ስለገባልን ዝክር አታቋርጡ የምንለው ስለዚህ ነው እኮ: ከሰባተኛው ቀን እስከ ሰባተኛው ዓመት ድረስ በምናደርገው ዝክር ምክንያት አምላክ በኪነ ጥበቡ ያቺን በሲኦል ያለች ነፍስ ቀስ በቀስ ከራስ ጠጉር እስከ ሙሉ አካል ድረስ እያወጣ በመጨረሻ ወደ ገነት መንግሥተ ሰማያት ያስገባታል በማለት ሰብከው ያሰናብቷቸዋል::

እኅታቸውን ከሲኦል ለማውጣት ድኅነታቸው እንደያዛቸው የተረዱት እናትም ያላቸውን ጥሪት ሸሽጠውና ተበዳድረው አንድ በግ በማረድ ከሥጋው አንዲት ቁራጭ ሳያስቀሩ ደጀ ሰላም ወስደው እንደሰጡና በዕለቱ ቁርባን ወይም በቅዳሴ የታጀበ ጸሎተ ፍትኃት እንደተደረገላቸው የዓይን ምሥክሮች ነን:: እናንተ በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል እናንተ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል እየተባለ ያለቦታው በሚጠቀስ ጥቅስ ብዙ የዋሆች ተታለው ያለክርስቶስ ጽድቅን እንደተጠሙ ኖረው ጽድቅን እንደተራቡ ያልፋሉ:: በወንጌል ጌታችን እንዳለው ሆኖብን ይሆን ? « እስመ ትበልዑ አብያተ መበለታት ወታመክንዩ ወታበዝኁ ጸሎተ ... እስመ ተዐጽዉ መንግሥተ ሰማያት ውስተ ገጹ ለሰብእ አንትሙሂ ኢትበውኡ ወለእለሂ ይበውኡ ትከልእዎሙ በዊአ » ( ማቴ 23 ፥13 - 15 ) ትርጉም « መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ ... በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ትበላላችሁ » እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በላ ቸው ::

በሲኦል የነበሩ ኃጥአን የቦታ ለውጥ በማድረግ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት የሚችሉባቸው በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ የምንሰብከው ብዙ ቢሆንም ከተዝካር ተጨማሪ ቅዳሜና እሑድን የሚያከብር የነበረ ነገር ግን ሲኦል የገባ ኃጢአተኛ በየሳምንቱ ቅዳሜና እሑድ ከነዲደ ሲኦል ያከብራቸው በነበሩት ቀናት እየወጣ ዕረፍት እንደሚያደርግ ይተረካል:: እንዲህ እንዲህ እያለ ጌታችን የሚመጣው በዕለተ ሰንበት እሑድ ነውና ያን ዕለት እንደወጣ ይቀርና መንግሥተ ሰማያት ይገባል እየተባለ በመሰበኩ ዛሬ በክርስቶስ ከማመን ይልቅ እነዚህ የመግቢያ መንገዶች ናቸው የተባሉትን ትምህርቶች ሕዝቡ ሌትና ቀን እየተማጸነ ይኖራል::

የገድለ ተክለሃይማኖት ጸሐፊም በመጽሐፉ ውስጥ በመደጋገም ያሰመረባቸው /ዓቢይ/ መልእክቶቹ « ዝክርህን መታሰቢያህን» ላደረገ ሁሉ እኔ እምረዋለሁ ብሏል ጌታችን በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የተዝካር ትምህርት ተባባሪ ለማድረግ ሞክሯል::

ገድሉ ያለምንም ፍረኃት « የሚቹን የተክለ ሃይመኖት የመታሰቢያ በዓል የዘከረ ሁሉ የዘካሪው 10 ትውልድ በዚያ ዝክር ምክንያት የዘላለም ሕይወት እንደሚያገኝና ጽድቅ እንደሚቆጠርለት ስሙም በሕይወት መጽሐፍ እንደሚጻፍ ይተርካል::ከዚህ የተነሳ 90 በመቶ የሚሆነው የቤተክርስቲያናችን ሕዝብ ሕይወቱ ተደግፋ የቆመችው እነዚህን ቅዱሳን ናቸው ተብለው የሚታወቁትን ሰዎች የመታሰቢያ በዓል መዘከርና ማክበር እንዲሁም የሚች ዘመድን ተዝካር ተበድሮና ተሰልቆ በማውጣት ላይ ነው::

ከላይ እንደገለጽነው ድኅነቱና ሁኔታው ያስገደዳቸው በጎጃም ክፍለ ሀገር የሚገኙት ምዕመናን በተዝካር ላይ የወሰዱት እርምጃ ተዝካር ለጽድቅ ምንም ጥቅም እንደሌለው በዚህም መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደማይቻል ያስመሰከረ ውሳኔ ነው:: ለመሆኑ በተዝካር ( የሚች ዘመድን ሆነ ጻድቅ እያልን የምንጠራቸው ሰዎች መታሰቢያ በማድረግ ) ጽድቅ ቢገኝ ኖሮ ለምን የአምላክ ልጅ ቅድስት ከምትሆን ከድንግል ማርያም በሥጋ ተወለደ ?

እያንዳንዱ በግሉ ከክርስቶስ ጋር በሚኖረው ኅብረት ተጠያቂ በሆነበት በአዲስ ኪዳን በአንድ ሰው ድግስ 10 ትውልድ የሚድንበት ሥርዓት ከየት እንደተገኘ ለጸሐፊዎችም ግልጽ የሆነ አይመስልም:: ጌታችን በወንጌሉ « በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም በእርሱ የማያምን ግን አሁን ተፈርዶበታል »

ሲል የዚህ ፍርድ ማጠቃለያ ወይም አመክሮ ተዝካር እንደሆነ ወይም ሰንበትን ማክበር ነው በማለት አልገለጸም ። ( ዮሐ 3÷ 17 - 18 )

## የመቃብሩን ሥፍራ የተሳለመ ይጸድቃል

ስለ ጸሐፊዎቹ ማንነት ሆነ የእምነት አቋም እንዲህ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው ፡ ምክንያቱም ጸሐፊዎቹ የሰው ልጅ ለመጽደቂያ መንገድ ይሆነዋል የሚሉት ተቆጥሮ የሚያልቅ አይደለም ። ሰዎቹ ስለ ጽድቅ ማለትም እግዚአብሔር በክርስቶስ ስቃይና መከራ አማካኝነት ጽድቅን እንደሠራላቸው ለሚያምኑ ሁሉ ጻድቅ ሆነው እንዲቆጠሩ የቸርነት ሥራ እንደሠራላቸው የማያውቁ ናቸው ባንልም ጽሑፋቸው በግልጥ እንደሚያስረዳው ግን ሆን ብለው በእግዚአብሔር ኀሳብ ላይ የተነሳሱ እንደሆኑ አፋችንን ሞልተን እንናገራለን።

«ስግደት የሚገባው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደእርሱ (ወደ ተክለ ሃይማኖት) መጣ ስግደት የሚገባትም እመቤታችን ድንግል ማርያምም አብራው ነበረች » ይላል ። ጸሐፊው ይህን አባባል ከየት እንዳመጣው ባይታወቅም እንዲህ አይነቱን የባዕድ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ አጠንክሮ ይቃወመዋል።

ለነገሩ የዚህ መጽሐፍ ወንድም የሆነው መስተብቍዕ ዘመስቀል «ለማርያምና ለዕፀ መስቀሉ የፈጣሪ ክብር ይገባቸዋል በክብር ከፈጣሪ ጋራ ተካክለዋልና» በማለት ድፍረትን ጽፎ የለ ?። በአንድነት በሦስትነቱ ተክብሮ የሚኖረውን ብቸኛ አምላክ ማርያምና ዕፀ መስቀሉ በክብር ይተካከሉታል በማለት የልዑል እግዚአብሔር ክብር የሆነው ክብር ይገባቸዋል ይለናል። ይህም ትምህርቱ የጸጋ የአክብሮት የሚለውን ትምህርት ጨርሶ በመጣል ክብረ እግዚአብሔርን እያፈሰ ደስ ላለው ያካፍላል ። ወደ ተነሳንበት ነገር እንመለስና እንደ ጸሐፊው ሃሳብ ፦

« ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ
ተክለ ሃይማኖት መጥቶ « አንተ ከተቀበርህበት
ቤተክርስቲያንህም በታነጸበት ቦታ የተቀበረ ሁሉ
በእኔ ዘንድ ዋጋ አለው ገሃነምንም አያይም »
አለው። ( 54: 12 )

እነዚህ አጽራረ ክርስቶስ የሆኑት ጸሐፊዎች በዚህ ስፍራ ደግሞ ሰው የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ተክለ ሃይማኖት የተባሉት ሰው የተቀበሩበትን ጉድጓድ ( የመቃብር ሥፍራ ) አፈላልጎ በእግር ሆነ በመኪና በፈረስ ሆነ በአየር በርሮ በመሄድ ከተሳለመው ገሃነመ እሳትን የጎሪጥ እያየ ወርቅ በወርቅ በሆነው ጎዳና ያለፍርኃት በነጻነት መንግሥተ ሰማያት ጥልቅ ማለት ብቻ ነው ይላሉ።

አስቀድመው ዝክሩን የዘከረ መታሰቢያውን ያደረገ ነው የሚጸድቀው ካሉን በኋላ በዚህ ያልተያዘላቸውን ሰው ደግሞ እንዳሻው ኖሮ በመጨረሻው ግን እንደምንም ብሎ የተክለ ሃይማኖትን መቃብር ፈልጎ በመሄድ ከሰገደ ጽድቅ እንደሚቆጠርለት ቃል ኪዳን አለው በማለት ድፍረታቸውን በሃይማኖት ካባ ሸፍነው ጽፈዋል።

ከመቃብር ጋር ያለው ግንኙነት ምንጩ ከየት ነው ?። መጽሐፍ « «ብዙኀ ሕማሞሙ ለጻድቃን ወእምኲሉ ያድኅኖሙ እግዚአብሔር እግዚአብሔር የዐቅብ ኵሎ አዕጽምቲሆሙ ወኢይትቀጠቀጥ አሐዱ እምውስቴቶሙ ... ... ትርጉም « የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው እግዚአብሔር ከሁሉ ያድናቸዋል እግዚአብሔር አጥንታቸውን ሁሉ ይጠብቃል ከእነርሱም አንድ አይሰበርም » አለ እንጂ ቅዱሳን የምንላቸውን አጥንት እያሰባሰበ ያሰግዳል አይልም።(መዝ 33፡ 20)

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለጣ ከመቃብር ጋር ግንኙነት ያደርጉ የነበሩት አጋንንት እንደሆኑ በግልጥ ሰፍሯል። (ማር 5፡2 ) 75 በመቶ የሚሆነው የቤተክርስቲያንችን አገልጋይ የሚኖርበት ቤት ራሱ ለሙታን አጽም ማሳረፊያ እየተባለ በቅጥረ ቤተክርስቲያን በሚሠሩ ቤቶች ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 74 በመቶው ፍርስራሽ የሙታን አጥንት የተከመረበት ነው።

ይህን የተለማመደ ጸሐፊ ስለ ጽድቅ ሲጽፍ የተክለ ሃይማኖትን መቃብር መሳለም ዋነኛ መንገድ ነው በማለት አስተምሯል። ይህም ስብከት ሥፍራ ይዞ እስከዛሬ በየዓመቱና አንዳንዶችም በየወሩ ቁጥሩ በርካታ ሕዝብ ተክልየ የተቀበሩበት ነው የተባለውን ሀገር ደብረ ሊባኖስን መቃብራቸውን በመሳለም ይገኛል። የተባለውንም የዘላለም ሕይወትና በረከት ለመቀበል ይጎርፋል። እንዲያውም ከጸሎት ቋመት የተነሳ አንዲት እግራቸው ተቆርጣ ነበር ስለሚባል ተቆርጣ የነበረችው እግራቸው ናት ተብላ በመስታወት የተቀመጠችን አጥንት በመሳለም ለመባረክ ሲጋፋ ቀላል ያልሆነ ሕዝብ እንደሚጎዳ የታወቀ ነው። ይህም በአሕዛብና በማያምኑት ዘንድ ዘላለም ሲያሰድበን ይኖራል።

ስለ መቃብር መሳለም ጉዳይ በቤተክርስቲያናችን ምን ያህል መናፍስት ቦታ እንደያዙ ለመረዳት አጥቢያ ነው የምንለውን ቤተክርስቲያን አተኩሩ መመልከቱ በቂ ነው:: በአንዳንድ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት የነገሥታት ሆነ ቅዱሳን እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች ፍርስራሽ አጽም ከመንበሩ ሥር ሆኖ ይህ የዋህ ሕዝብ ቀን ከሌሊት እየሰገደላቸው እየተሳለማቸው ይሄዳል ::

ለመረጃ ያህል በራስ መኮንን ተተከለ በሚባለው በሐረሩ ተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን ከመንበሩ ፊት ለፊት የራስ መኮንን ነው የተባለ አጽም በዕብነ በረድ ተሠርቶ በመቀመጡ ምዕመኑ የሚሳለመውና የሚሰግደው ይህን የፈረሰ አጽም ማጥን ነው:: ለመሆኑ ሕያውን አምላክ እናመልካለን እያልን የሙታንን አጽም አቁመን የምንሰግድ ይህ ድብልቅ አምልኮ የአሕዛብ የአምልኮ ሥርዓት አይሆንብንም?:: ይህም ብቻ አይደለም ፡ በመዲናችን በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው ካቴድራል ቅደስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ክርስቲያን ለመሆናቸው እንኳ በቂ መረጃ የሌላቸው የነገሥታት አጽም መንበሩ በሚገኝበት አቅጣጫ የታችኛው ክፍል በመቀመጡ ሕዝቡ በአጽሙና ወደ አጽሙ አቅጣጫ እንዲሰግድ ተደርጓል:: ከየት የተቀዳ ትምህርት ይሆን ? ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለኃይለ ሥላሴና ቤተሰባቸው ፣ በዓታ ለዓጼ ምንሊክና ቤተሰባቸው አጽም ማሳረፊያ ሆኖም ይታያል አሁንማ የጀኔራሎች፣ ለካድሬዎቱ ለከሚኒስቶች ወዘተ አጽም ማረፊያ ሆናለች ቤተክርስቲያን ::

ይህን ልማድ ነው ጸሐፊው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግፎታል የሚለን:: ሴቶች የመድኃኒታችንን ቅዱስ ሥጋ ሽቶ ለመቀባትና ለማየት ወደ መቃብሩ በሄዱ ጊዜ ቅዱሳን መላእክት ይህን ሥራቸውን ግሣጼ በተሞላበት መልኩ እንደተናገሯቸው ልብ ማለት ያሻል:: « ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ ? » አሏቸው እንጂ ጎሽ በርቱ መቃብሩን ተሳ ለሙ በረከትም ከመቃብሩ ታገኛላችሁ አላሏቸውም:: (ሉቃ 24፡ 5 )

ጸሐፊ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ግን « ጌታችን ወደ ተክለ ሃይማኖት መጥቶ ከሩቅም ሆነ ከቅርብ ማንም ሰው ወደ መቃብርህ የሄደውን ( የመጣውን ) እኔ (ኢየሱስ) ወደ መቃብሬ ኢየሩሳሌም እንደሄደ እቆጥረዋለሁ » አለው በማለት በአምልኮ መቃብር ተባባሪ ሊያደርገው ሞክሯል:: ( 54፡ 10 )

ለመሆኑ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄደ መቃብሩን እንዲሳለም አስተምሯልን ? ተከታይ

ደቀመዛሙርቱስ ? እነርሱን የተከሉ አባቶችስ ? እንዲያውም ጌታችን በጥንት ይደረግ እንደነበረው ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ በሰሎሞን ቤተ መቅደስና በየተራሮች ላይ ይደረግ የነበረውን ስግደት እያለ መኳተን ከእንግዲህ እንደቀረ ለሳምራዊቷ ሴት ሲያስተምር :-

« ወይቤላ ኢየሱስ እመንኒ ብእሲቶ ከመ ትመጽእ ሰዓት አመ ኢበዝንቱ ደብር ወኢበኢየሩሳሌም ዘይሰግዱ ለአብ አንትሙሰ ትሰግዱ ለዘኢተአምሩ ወንሕነሰ ንሰግድ ለዘናአምር እስመ መድኃኒት እምነ አይሁድ ውእቱ ወባሕቱ ትመጽእ ሰዓት ወይእዜ ይእቲ አመ እለ በርቱዕ በአማን ሰጋድያን ይሰግዱ ለአብ በመንፈስ ወበጽድቅ እስመ አብኒ ዘከመዝ የኀሥሥ እለ ይሰግዱ ሎቱ »

ትርጉም

« በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል:: እናንተ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ: እኛ ግን መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንደሰግዳለን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል:: አሁንም ሆኗል: አብ ሊሰግዱለት እንደነዚህ ያሉትን ይሻልና «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል » በማለት ትክክለኛ ትምህርተ ሥግደትን በአጭርና በግልጽ ቋንቋ አስፍሯታል::

በዚህ በጌታችን ትምህርት :-

1. ከእንግዲህ በኢየሩሳሌም ሆነ ምክንያት እየተፈለገ በየተራሮች ይደረግ የነበረው ስግደት እንደቀረ ፣
2. ስግደት የሚሰጠውም መዳን ከሆነበት ከአይሁድ በሥጋ ለተገለፀው ለክርስቶስ እንጂ ለማይታወቁ ወይም መድኃኒት ላልሆኑ አማልክት ወይም ሰዎች እንዳይደለ፣
3. እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ስግደትም በመንፈስና በእውነት ብቻ እንደሚደረግ
4. አብም ይህን ስግደት እንደሚፈልገው ፣
5. እንሰግዳለን የሚሉትም ጌታችን ባስተማረው መሠረት ብቻ እንዲያደርጉ አስተምሯል::

ይህ የክርስቶስ ትምህርት ያልተዋጠላቸው ደራስያን ቢያስፈልግ ስግደት የአክብሮት የጸጋ የባሕርይ ተብሎ ይከፈላል በማለት የአክብሮት

ካረቤቶቻችን ለዘመዶቻችን ሰዎች የምንሰጠው ሰላምታ የጸጋ ለመቃብር ሥፍራ ለሙታን አጽም ለሕንጻ ቤተክርስቲያን ፣ ለዕፀ መስቀል ለመላእክትና ቅዱሳን እያልን ለምንጠራቸው ሰዎች ምስል ወ.ዘተ. ብለው እያሉ የጌታችን ትምህርት ያንሳልና አስተካክለነዋል በሚል ስሜት ይናገራሉ::

ክብር ይሁንለትና ለስም አጠራሩ ለትምህርቱ ሕጸጽ ፣ ለአነዋወሩ ነቀፋ፣ ለንግግሩ ስሕተት የሌለበት ጌታ ስለ ስግደት ሲያስተምር « ለሙታንና ለመቃብር ለምስልና ለቅርጽ መስገድ ቢያስፈልግ ኖሮ እነ መምሬ እንዳሉት የጸጋ ስግደት «ስገዱላቸው» ብሎ ለማለት ጊዜም ቃላትም አላነሰውም ነበር:: እርሱ እንዳለው የምናውቀውን እንናገራለን የሰማነውን እንመሰክራለን ነበር ያለው:: ( ዮሐ1:11 )

እርሱን የሃይማኖቱ ጀማሪና ፈጻሚ ሊቀ ካህናት መምህር አድረጎ የተቀበለ ክርስቲያን መምህሩና መሪው ባስተማረው ላይ ቅንጣት ያህል አይጨምርም ቅንጣት ታህል አይቀንስም :: ዳሩ ምስክርነታችንን አትቀበሉትም እንዳለው የመድኃኔዓለም ትምህርት ጆሮን የሚያሳክክ የሆነባቸው ደራስያን ክታበ አጋንንት ለመቃብርና ለፈረሰ አጽም ስግደት እንዲደረግ ባደረጉት የረጅም ዓመት ስብከት እነሆ ይህ ተሳክቶላቸው « ለአንዲት እግር ቁራጭ ሰው ሁሉ በደብረ ሊባኖስ እየተጋደለ ነው::

መጽሐፍ « ከመ ለስሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ይስግድ ኵሉ ብርክ ዘበሰማያት ወዘበምድር ወበቀላያት ወእለታሕተ ምድር... » ይለናል:: ( ፊል 2: 10

# ፍርፋሪ የበላ ይጸድቃል

በመግቢያችን ላይ እንዳልነው እነዚህ ሰዎች ( ጸሐፊዎች ) መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ተቆጥሮ የማያልቅ በር አላቸው:: አስቀድመው መቃብሩን መሳለም ለመንግሥተ ሰማያት መግቢያ እንዲሆን እግዚአብሔር ቃል ገብቶለታል ካሉን በኋላ፣ አሁን ደግሞ በየወሩ ሆነ በየዓመቱ ለተክለ ሃይማኖት እየተባለ ከሚደረግ የጠላና የእንጀራ ድግስ ፍርፋሪ ወድቆ ያገኘና የበላ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ችግር እንደሌለበት ይናገራል::

ስለ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ እውነተኛው መምህር ክርስቶስ ሲያስተምር « እኔ የበጎች በር ነኝ ... በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል በማለት ሌላ ተጨማሪ የመግቢያ መንገድ እንዲሆን እነ እከሌ አሉ ሳይል

አስተምሯል::(ዮሐ10:9) በዮሐ 10:1 ላይም በበሩ የማይገባ እርሱ ሌባ ነው በማለት በጸሐፊዎቹ የሚተረከልንን አማራጭ በሌባ መስሎ የተናገረው::

ለሐዋርያው ፊልጶስም ሲመልስ እኔ መንገድ ነኝ አለው እንጂ በቅዱሳኑም በመላእክትም ይገባል አላለውም( የሐ 16:6 ) እነ ጸሐፊ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ግን :

« ወለእመ ኢረከበ ቁርባነ ይብላዕ ፍርፋራተ ዘወድቀ እማዕደ ተዝካርከ እነ ኢየሱስ ቃልየ ዘኢይሄሱ ..... ወአረፍቆ ምስሌከ በውስተ መንግሥትየ በእንተ እምነቱ

ትርጉም

« ቅዱስ ቁርባንን ባይቀበል ከመታሰቢያህ ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ቢበላ እኔ ኢየሱስ ቃሌ የማይታበለው ስለእምነቱ በመንግሥተ ሰማያት ከአንተ ጋር አኖረዋለሁ »

እያሉ እግዚአብሔር ለጽድቃትን የከፈተውን በር ክርስቶስን ሕዝቡ እንዳያውቀው አድርገዋል::

እንዲህ አይነቱ ልምምድ ዛሬም በደብረ ቁስቋም ማርያም ቤተክርስቲያን ይሰራበታል « ለመታሰቢያዋ ተብሎ የተቀቀለ ባቄላ ግልፋፊ ( ሽፋን ) መሬት ወድቆ የበላ ሳይቀር ከተለያየ በሽታ እንደሚፈወስ አጋንንትም እንደሚወጡለት ይነገራል:: ይህም ምን ያህል የከፋዎች ትምህርት በቤተክርስቲያናችን ሥር እንደሰደደ ያመለክታል:: ሊያስቅ ቢችልም ድርሳነ ማኅየዊ እየተባለ በሚታወቅ መጽሐፍ « ለመድኃኔዓለም ተብሎ ዝክር ሲደረግ ለጠላ የሚሆነው እንኩሮ ሲነኮር የእንኩሮው ሽታ የሸተተው ሰው እስከ ሰባት ቤት ድረስ ኃጢአቱ እንደሚማርለት ያለ ሐፍረት አስፍሯል::

ምዕመናን ሆይ ጽድቅ እንዲህ ዝክር በማድረግ ፣ የሞቱ ሰዎችን አጽም ና የመቃብር ሥፍራ በመሳለም እንዲሁም ለዝክር ሲባል በተነኮረ እንኩሮ ሽታ በጥቅሉ የ7ና የ10 ቤት ኃጢአት የሚያስወግድ ከሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ለምን

በሥጋ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ? ለምንስ መከራን ተቀበለ ? እናስተውል / እንኪንስ በዚህ ቀርቶ ሕግን ጠብቀን እንጸድቃለን የሚሉትን አይሁድን ቅዱስ ጳውሎስ « በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል» በማለት ነበር የገሰጻቸው:: (ገላ5:4)

# « የተክለ ሃይማኖት ተቅማጥ »

## የደፋሩና የከሐዲው ጸሐፊ ጉድ

ብዙ ሰዎች የገድላ ገድል ጸሐፊዎችን በጅምላ ሲፈርጁ መጻሕፍትን መረዳት የተሳናቸው አላዋቂዎች ናቸው በማለት ይናገራሉ:: በእርግጥ ጥቂቶች እንዲህ ቢሆኑም አብዛኞች ግን ስሕተተኞች ብቻ ሳይሆኑ ደፋሮች ከሃዲዎችና የሰይጣን አጋፋሪዎች ናቸው ለማለት እንደፍራለን::

ሰዎቹ ሆን ብለው በእግዚአብሔር የዘላለም እቅድ ላይ አይቻላቸውም እንጂ ቢሆንላቸው ማጥፋት ካልሆነም ሕዝብን በማሳሳት የሰይጣንን ድርሻ ማበራከት ተሰጥተው የተነሱበት ዓላማቸው ነው:: ስለሆነም ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በክርስቶስ የመስቀል መከራ ላይ በጠላትነት መነሳት፣ ክቡር ደሙን ማክፋፋት፣ ቅዱስ ሥጋውን ማራከስ፣ ስመክርስቶስን ማስካድ፣ ከሕዝቡ ኅሊና ማስረሳት በፈጠራና በአጋንንታዊ ትምህርቶች የሕዝቡን ኅሊና መያዝ ዋና ዋና መንገዳቸው ነው::

ደፋሮችና ከሐዲ የሆኑት እነዚህ ጸሐፊዎች በአንዱ በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ወደ ዓለም ገብቶ የነበረውን ኃጢአት ለማስወገድ እግዚአብሔር ይበጃል ያለውን አንድ ልጁ ክርስቶስ በደሙ ፈሳሽነት ያደረገውን ሥርዬት ዋጋ ለማሳጣት በገድሉ /ምዕራፍ 54 : 23/ ላይ እንዲህ በማለት ጥፈዋል::

ጌታችን ወደ ተክለ ሃይማኖት መጥቶ :-

« ወናሁ ትመውት በሕማመ ብድብድ በእኩይ ሞት ወእሬሲ ለከ ኪያሃ ከመ ስቅለትየ ወከመ ደመ ሰማዕት እለ እምቅድሜከ አኮ ለባሕቲትከ አላ ደቂቀ ከኒ እለ ይመውቱ በሕማመ ብድብድ በውስተ ዛቲ ገዳም እኌልቆሙ ምስለ ሰማዕታት ወአወፍዮሙ ለከ በመንግሥተ ሰማያት ... »

« እነሆ በክፉ ሞት በተቅማጥ ትሞታለህ፣ እሷንም እንደ ስቅለቴና ከአንተ በፊት እንደነበሩት ሰማዕታት ደም እቆጥርልሃለሁ ነገር ግን ለብቻህ አይደለም በዚች ገዳም በተቅማጥ በሽታ የሚሞቱትን ልጆችህንም ቁጥራቸውን ከሰማዕታት ጋራ አደርጋለሁ በመንግሥተ ሰማያትም ለአንተ እሰጣቸዋለሁ ... » ብለዋል::

ይህን የምታነቡ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላችሁ ወገኖቻችን እንዲህ ያለ የተረገመ ጽሑፍ ያለበትን መጽሐፍ ይህ የዋህ ሕዝብ ለበረከት እንዲሳለመውና ሰውነቱን እንዲያሻሽበት እየተባለ ተሰውሮ ባላወቀው መንገድ ከመርገም ሥር እንዲወድቅ መደረጉን በማሰብ ከእንባ ጋር መጸለይን እንዳትረሱ አደራችን ታላቅ ነው።

ከቅዱስ አምላካችን ለይቶን የነበረውን ኃጢአት የቅዱሳን ሰዎች እንባ ጾምና ጸሎት ባለመቻሉ ሁሉ በእርሱ ዘንድ የሚቻል አምላክ በተወደደ ልጁ ደም ኃጢአታችንን እንዳነጻው ሐዋርያቱ አስረግጠው ጽፈውልናል። ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሲገልጽ « ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር በክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ» ሲል ቅዱስ ጳውሎስም « የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ፣ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፣ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» በማለት ለዚህ ደም ክብር እንድንሰጥ ጽፎልናል።

ይህን ታላቅና የከበረ የክርስቶስ ደም ነው ጸሐፊዎቹ ከአንድ ተራ ሰው ተቅማጥ ጋር እኩል አድርገው « ተቅማጥህ እንደ ስቅለቱ ደም ነው » ብሎታል በማለት የሚናገሩት። ይህን ተቅማጥ ( አሜባ ብለው ተርጉመውታል) ዐርብ ዕለት ከፈሰሰው ለዓለም ኃጢአት ማስተስረያ ከፈሰሰው የጌታ ደም ጋር አስተካክለው ያስተማሩት ። ምዕመናን በክርስቶስ ደም መፍሰስ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኙ ከማስተማር ይልቅ እንደ ተክለ ሃይማኖት በተቅማጥ የሞተ ሁሉ ተክለ ሃይማኖት ገቡበት ወደ ሚሉት እንደሚገቡ በገድሉ ላይ አስቀምጠዋል ።

« በዚህ ገዳም ( በተክለ ሃይማኖት ) በተቅማጥ በሽታ ( አሜባ) የሚሞቱ ባንተ የታመኑ ልጆችህ ሁሉ ቁጥራቸውን ከጻድቃንና ከሰማዕታት ጋር አደርጋለሁ በመንግሥተ ሰማያትም ለአንተ እሰጣቸዋለሁ » ብሎ ጌታ ቃል ገብቶለታል በማለት ጽድቅ በተቅማጥ በሽታ ነው ይሉናል።

ይህም ትምህርታቸው ዛሬም በዋልድባ ገዳም ተመሳሳይ ይዘቱን የጠበቀ ልማድ ይታያል። በዋልድባ ገዳም ማንም ሰው ሲገባ በመጀመሪያ በንዳድ ( በወባ) ካልታመመ የገዳሙ መንፈስ ( ቃል ኪዳን ) እንዳልተቀበለውና በረከተ ገዳሙ እንደማይደርሰው ስለሚነገር ጻድቅ ለመሆናቸው እግዚአብሔርም

በገዳሙ እንዲኖሩ ለመፍቀዱ የግድ በንዳድ ታመው መታየት የግድ ይላል:: በልማድም ገዳሙን የመሠረተው ጌታችን ነው ስለሚባል ዋልድባ ዛሬ የጻድቃን ገዳም እንደሆነ ይወራለታል:: ስለገዳሙ ታሪክ በጋዜጣችን ተከታተሉ::

እንደ ገድለ ተክለ ሃማኖት ደራሲ አባባል በተገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት በአባ ተክለ ሃይማኖት ገዳም የነበሩ ሰዎች ሁሉ በተቅማጥ በሽታ ወዲያውኑ ተያዙ ( 54: 27 ) ይህ በሽታ የጽድቅ ቃል ኪዳን ስለሆነ በምዕራፍ 54 ቁጥር 30 ላይ የተቅማጥ በሽታ አምጪ የሆነችውን ተኀዋስ ተክለ ሃይማኖት እንዲህ አሏት :: « ጻድቁን እንጂ ኃጥኡን አትንኪ » አላት በማለት በተቅማጥ የተያዙት ሁሉ ጻድቃን ነበሩ በማለት ጽፏል :: ይህን የተረገመ የአጋንንት ትምህርት ሰዎች ሁሉ በማወቅና በመንቃት የክርስቶስን ደም ከማክፋፋትና የባሰ ቅጣት ከመቀበል እንድን ዘንድ ጽፈናል::

# የሸዋ ሰው የመዳን ተስፋ

መቃብሩን የተሳለመ ሁሉ እንደሚጸድቅ የተናገሩት ደራስያኑ በዚህ ስፍራ ደግሞ ሥዕላዊ ድርሰቱን እንዲህ ያቀርበዋል:: የተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር የሆኑ ሁለት ሰዎች የነፍሳቸውን ድኅነት ፍለጋ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ ይላል:: አንባቢ ልብ ሊለው የሚገባው እዚህ ላይ ነው:: አስቀድሞ በገዳሙ ያሉና በተቅማጡ የሚያዙት ሁሉ እንዲሁም በገዳሙ የሚኖሩ ሁሉ በተክለ ሃይማኖት ቃል ኪዳን ርስተ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያገኙ መናገሩን የረሳው ደራሲ ከዚያው ገዳም ድህነት ያላገኙ ርስተ መንግሥተ ሰማያት ያልገቡ እንደሆነ አድርጎ አቅርቧቸዋል:: ይህም የሚያሳየው እንደደራሲው ሐሳብ በገዳሙ መገኘት ሆነ የተክለሃይማኖት ተዝካርን ማውጣት ወይም በገዳሙ ሆኖ በንዳዱ መያዝ ያጸድቃል የሚለው ትምህርት እንዳላሳረፋቸው ነው::

ድኅነተ ነፍስ ፍለጋ ያውም በአዲስ ኪዳን ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ የተባሉት ሰዎች ኢየሩሳሌም እንደደረሱና የኢየሩሳሌም ጳጳስም ከየት ሀገር እንደመጡ እንደጠየቃቸው እነርሱም ከኢትዮጵያ እንደመጡ እንደመለሱለት አስፍሯል:

ጳጳሱም ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን ባወቀ ጊዜ « የተክለ ሃይማኖትን መቃብር ታውቃላችሁን ? አላቸው እነርሱም « የመጣነው ከዚያ ነው » አሉት ይላል:: ሊቀ ጳጳሱም የመጣነው ከዚያ ነው ማለትን በሰማ ጊዜ ተነስቶ

ስገደላቸው እግራቸውንም ሳመና ለምን እንደ መጡ ሲጠይቃቸው « የነፍሳችንን ድኅነት ልንሻ » አሉት:: ሊቀ ጳጳሱም « ሰው የነፍሱን ድኅነት ሳያውቅ ለካ ይጎዳል» ብሎ ጮኸ» በማለት ደራሲዎቹ አስፍረውልናል::

ይህ ሊቀ ጳጳስ በኢየሩሳሌም ያውም የዓለም መድኃኒት ክርስቶስ በተወለደበት፣ ባደገበትና በተሰቀለበት በተቀበረበትና ባረገበት የተሾመ ነው:: ታዲያ መቃብር መሳለም የሚያሳርፍና ርስተ መንግሥተ ሰማያት የሚያስገባ ቢሆን ከተክለ ሃይማኖት ይልቅ የጌታችን መቃብርን መሳለም ሺህ ጊዜ አይበልጥም ነበርን ?

ይሁን ብለን እንኳ ብንቀበለው ከተክለ ሃይማኖት መቃብር መጣን ሲሉት ወድቆ መስገዱና እግራቸውን መሳለሙ ምን የሚሉት ትምህርት ነው:: እንደኛ ሰዎች አባባል የጸጋ የተባለው ስግደት እምን ድረስ እንደሆነ ሊገምት አይችልም:: ይህም ሰይጣን ያጣውን የደቂቃ ስግደት በተክለ ሃይማኖት ሽፋን እየከሰከሰ እንደሆነ ለማገንም ግልጽ የሆነ ይመስለናል::

ተክለ ሃይማኖት በነበሩበት ዘመን የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ የነበረው ማን እንደነበር በውል ባይታወቅም ጸሐፊዎች እንደሚሉት ግን ጽድቅ በክርስቶስ እንደሆነ ያልገባው የመቃብር አፈር እያፈላለገ የሚሰግድ ሰው እንደነበር ልንረዳ እንችላለን:: እንግዶቹ ሰዎች ኢየሩሳሌም ድረስ የመጡት የነፍሳቸውን ድኅነት ለመፈለግ እንደሆነ ሲነግሩት « የነፍሳችሁ ድኅነት የተክለ ሃይማኖት መቃብር ነው » አላቸው የሚለው አባባል በእርግጥ በአዲስ ኪዳን የኖረና የተሾመ ጳጳስ ሰው ነው ለማለት አንደፍርም::

ሆኖም ደራሲዎቹ ዛሬም እንኳ ኢየሩሳሌምን እንደ እግዚአብሔር ለሚቆጥረው ሕዝባችን ወንጀላቸውን ከቅድስት ሀገር አስተሳሰብ ጋር አቀናጅተውታል:: በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ዛሬም ወንጀል እንደሚሠራ የታወቀ ነው:: ከግቢያቸው ቧንቧ የቀዱትን ውኃ ፣ እዚሁ መርካቶ የተሠራ የብረት መስቀል ፣ ወጣ ብለው ከሀገራችን የዛቁትን አፈር ከኢየሩሳሌም የመጣ ለበረከት ይሁን እየተባለ ስንቱ ተታሏል:: እስከ ዛሬ ተችሏቸው ይሆናል ከእንግዲህ ፀሐይ ወጥቶባቸዋልና አይቻላቸውም :: እግዚአብሔር ትውልድ አስነስቷልና::

# የሙታን መንፈስ ግንኙነት

በኢየሩሳሌም ነበረ የተባለው ሊቀ ጳጳስ ለእንግዶቹ « በተክለ ሃይማኖት መቃብር ላይ መንፈስ ቅዱስ ዘወትር ይረባልና ( ይሰፋልና) ተመልሳችሁ ወደ ሃገራችሁ ሂዱ ያለመቃብሩ መዳን ተስፋ የላችሁም » አላቸው ። ምክንያቱንም ሲገልጽላቸው « በተክለ ሃይማኖት መቃብር የተቀበረ በሁለተኛው ቀን መንግሥተ ሰማያት ይገባል ብሎ ጌታችን ለተክለ ሃይማኖት ቃል ኪዳን ገብቶለታል፡ በማለት የገድሉ ደራሲዎች ወንጀላቸውን በሃገር ውስጥና ከሃገር ዉጪ ድጋፍ ያለው ነው ለማለት ደፍረዋል።

ደራሲዎቹ ስለ ተክለ ሃይማኖት መቃብር ምን እንዳተጋቸው ባይታወቅም በገድሉ ውስጥ ሰፋ ያለ የትረካ ሥፍራ ሰጥተውታል። (59 ፡ 1)

አንድ ወታደር ሁለት መነኩሳትን አግኝቶ ሰላምታ ከሰጣቸው በኋላ መነኩሳቱ ወታደሩን ከየት እንደመጣ ሲጠይቁት ከሸዋ ክፍለ ሃገር ግራርያ ከምትባል ሥፍራ ( አሁን ደብረ ሊባኖስ) እንደመጣ ገለጸላቸው። እነርሱም ተክለ ሃይማኖትን ታውቀዋለህን ? ወደ መቃብሩስ ደርሰሃልን ? አሉት ። ይላል ገድሉ ። ሰውየውም ተክለ ሃይማኖትን አውቀዋለሁ ከመቃብሩም ደርሻለሁ ባለቸው ጊዜ መነኩሳቱ ፈጠን ብለው ተነስተው ወድቀው ሰገዱለትና የእግሩን ትቢያ ይልሱ እጁንም ይስሙ ጀመሩ በማለት አንባቢያቸውን ባዕድ አምልኮ እያለማመዱ ስግደትን ከእምላክ ውጪ በወታደሩ ለመሰሉት መንፈስ ሲያቀብሉ እንደኖሩ ያስረግጥልናል።

ይህን ስናጠናው የደራሲዎቹ ዋና ዓላማ በአንድም በሌላም እግዚአብሔርን ለማስቀናት በመንፈሳዊ ስምና ሽፋን የተዘጋጀውን ድብቅ የሰይጣን ዓላማ ለማስፈጸም እንደሆነ ተረቱ ያስረዳናል።

ጠላት ሰይጣን ጌታችንን በፈተነው ጊዜ « ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ » በማለት የዓለምን ሀብትና ክብር እንዳሳየው ጌታችን ግን « ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታ ለአምላክህ ብቻ ስገድ ተብሏል በማለት ሰይጣን ለማይክሮ ሰከንድ ለምትፈጸም ስግደት የዓለምን ክብርና ባለጠግነት ቢሆን ክፍሎ ለማግኘ ት የቋመጠውን ሲያሳፍረው እነ ደራሴ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ግን በየምክንያቱ በመቃብሩ በአጥንቱ እያመካኙ ሰይጣን በጌታችን ያፈረበትን እነሱ እያረኩት ይገኛሉ።

እንግዲህ ይህ በተክለ ሃይማኖት መቃብር የደረሰ እግር ሁሉ በረከት አለው የመዳን ተስፋችሁም የተክለ ሃይማኖት መቃብር ነው እያለ የሚያስተምር መጽሐፍ የቤተክርስቲያናችን ሀብት ተብሎ ይከራበታልን ? የሚገርመው ዛሬም በቤተ መቅደስ ዓውደ ምህረት ይህንኑ መጽሐፍ ይዘውና አንግበው እየጠቀሱ የሚያስተምሩ ሰዎች መገኘታቸው ነው፡፡ ስለ ነፍሳቸው ድኅነት ለሚጠይቁንስ ሰዎች መቃብር መሳለም ነው ብለን መናገር ቀርቶ ሊታሰብስ የሚገባው ነውን ? እውነተኛው መምህር ሐዋርያው ጳውሎስን ስለ ነፍሱ ድኅነት ምን ላድርግ ባለው ጊዜ ፡- ሲመልስለት « ሐዋርያት የተቀበሩበትን እመቤታችን ድንግል ማርያም የተቀበረችበትን አብርሃም ይስሐቅ የተቀበሩበትን ወ.ዘ.ተ መቃብር ፈልገህ ተሳለም ወይም መታሰቢያቸውን አድርግ ሳይሆን ያለው « በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ » ነበር ያለው ( የሐዋ 16 ፡ 31 )

ተረቱ ይቀጥልና ለዚህ ወታደር እንዲህ አሉት « የተክለ ሃይማኖት አጽም ካረፈበት ቦታ ቁርባን የተቀበለ ሁሉ ሲኦልን አያይም » ሲል ከጌታ እንደበት ሰማን በማለት ውሸትን በእውነት አምላክ ላይ ተናግረዋል፡፡ እንዲያውም አሉ መነኮሳቱ የሸዋ ሰው መሆኑን ከተረዱ በኋላ « የሸዋ ሰዎች ያለ ተክለ ሃይማኖት መቃብር የመዳን ተስፋ የላቸውም » በማለት ተናግረውታል፡፡

መጽሐፉ የውሸት የፈጠራ ታሪክ እንደሆነ ራሱን በራሱ ያጋልጣል መጽሐፍ ክርስቶስ ለዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደመጣ እየተናገረ ደረሲዎቹ ግን « ለሸዋ ሰዎች መዳን የተክለ ሃይማኖት መቃብር ነው ተስፋቸው » በማለት ለየሀገሩ የመዳኛ መንገድና ምክንያት ያበጃሉ፡፡

ጸሐፊዎች ስለ ተክለ ሃይማኖት መቃብር ገናናነትና ክብር ብዙ መጻፍ እንችል ነበር በማለት በዕዳ ላይ ዕዳ ለመጨመር ችግር እንደሌለበት ያትታል ሆኖም ይላል ለሰሚዎች እንዳይበዛ ተውነው ይለናል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም መቃብሩ አማላጅ እንደሆነ ለተከታዮቹ በግልጽ ያስተምራል ፡፡« ወሀበነ ዝንቱ መካነ መምሕጸነ መቃብሪሁ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት » ትርጉም « መማጠኛ ( አማላጅ) የሚሆነንን ይህን የአባታችንን የመቃብር ቦታ እግዚአብሔር ሰጠን » ይላል ( 61 ፡ 10 )

አብሾ ባዞረው *ሥራሥር* ባናወጠው መንፈስ አጋንንት በተጠናወተው ኅሊና አስቦና አቅዶ ስለሚጽፍ በአንደኛው ቦታ ምን እንደጻፈ እንኳ ሳይረዳው በሌላው ላይ ምን እንደሚጽፍ ማሰብ ለእርሱ ቅዠቱ ነው ፡፡ ተቆጥሮ የማያልቅ

አማላጅ ባለቤት የሆነውን ተከታይ ሕዝባችንን በዚህ ጽሑፋቸው ደግሞ መቃብር አማላጅ ነው በማለት ተጨማሪ አደርገውለታል። ይህም ብቻ አይደለም በመጽሐፈ ዚቅ ላይ ሰንበትም አማላጅ ናት የሚል ዕዳ ተጽፎልናል።

እውነተኞቹ አባቶቻችን ሐዋርያት ጌታችን አደራ የሰጣቸውን የድኅነት ወንጌል ሰብከው ለትውልድ ሲያስተላልፉ እንዲህ ያለ ክኅደትና ወንጀል አልጻፉም ነበር ። ስለ መዳን ሲያስተምሩም የእኛዎቹ መናፍቃን እንዳሉት በብዙ አማላጅ በብዙ መንገድ ይጸደቃል መንግሥተ ሰማያት ይገባል ብለው አልተናገሩም። እንዲያውም በብሉይ ኪዳን ስለነበረው የአማላጅነት ሥርዓትና ሕግ ከገለጡ በኋላ « እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት ( አማላጆች ) የሆኑ ብዙዎች ናቸው እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል » በማለት ወደ እግዚአብሔር ሆነ ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት እግዚአብሔር የሚቀበልበት መንገዱና መካከለኛው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ የገድልና የድርሳን ጸሐፊዎች እንደሚተርቱት ፍጡራን ሰዎች ወይም መቃብራት አልያም ሰንበትና የወር በዓላት አማላጆች ናቸው የሚለው ፈጠራና የሆድ መሙያ አይደለም።

ፀረ ወንጌል ደራሲዎች እንደ እሥራኤል ከንቱ መሪዎች ሕዝባችንን በየምክንያቱ የባዕድ አምልኮን ትምህርት እያስተማሩ የሚኙ አጥንትን እያሳጠኑ መቃብርንና የተተከለ ሐውልትን እያጠኑ እያሳጠኑ እያሳለሙ የአምልኮ አመንዝራነትን አስፋፍተው በረከተ እግዚአብሔር ርቆን እነሆ ለዘመናት እያለን እንደሌለን እየሠራን እንዳልሠራን ራኃብተኞችና ስደተኞች ሆነን እንኖራለን።

# አጥንቱንና ሥጋዩን ዳስ

ስለ ተክለ ሃይማኖት ደራሲው እንደገለጠው እጅግ የሚዘገንን ነገር በመጽሐፉ ሞልቶበታል። በምዕራፍ 62 ላይ ተክለ ሃይማኖት ከሞቱ 57 ዓመት በኋላ የካቲት 19 ቀን ሕዝቅያስ ለሚባል ሰው ተገልጠው እንዲህ አሉት ይሉናል :-

ገድለ ተክለ ሃይመኖት ዘእሑድ
ምዕራፍ ፷፪

፩. እስመ ናሁ በጽሐ ዘመን ዘይቤለኒ እግዚእየ ከመ ያፈልሱ ሥጋከ ደቂቅከ እምዝየ በደኀሪ መዋዕል ወናሁ ለከ ሐረየከ እግዚእ ከመ ትግሥሥ ሥጋየ ወአዕፅምትየ

፫. ወይእዜኒ ተንሥእ ወአድሞሙ ለኲሎሙ ደቂቅየ ይትጋብኡ እምርትቅ ወእምቅሩብ፡ እስከ ዕለተ ፍልሰትየ አመ ፲ወ፪ ለወርኃ ግንቦት ዘውእቱ ዕለተ በዓለ ትንሣኤሁ ወበዓለ ሚካኤል ፍቁርየ

፬. ወአንትሙኒ ግበሩ በዓለ መንፈሳዊተ በስብሐት ወበጸሎት በቅዳሴ ብዙኅ ዘከመ ዕረፍትየ ተፈሥሑ ወቀደሱ መላእክተ ሰማይ ለእግዚእ ኲሉ ስብሐት በዕለተ ሞትየ

፯. አእምር ጊዜ ምጽአትየ አዕፅምትየ አዑድ ፫ተ ጊዜ ቅድመ መንበረ ታቦት

፰. ወሶቤሃ ይበርህ ማኀቶት ዘጠፋአ ..

ምዕራፍ 62፡ 1- 8

ገድለ ተክለ ሃይመኖት ዘእሑድ
ምዕራፍ ስሳ ሁለት

2. በኋለኛው ዘመን ስለዚህ ስፍራ ( ደብረ ሊባኖስ) ልጆችህ ሥጋህን ያፈልሳሉ ያለኝ ዘመን እነሆ ደርሷልና አጥንቴንና ሥጋየን ትዳስስ ዘንድ ጌታየ እነሆ አንተን መርጦሃልና ለምን ትዘገያለህ?

3. አሁንም ተነስተህ ልጆችህን ሁሉ ቀጠራቸው እስከምፈልስበት የግንቦት ወር 12ኛ ቀን ይኸውም የእግዚአብሔር የትንሣኤው በዓል ቀን በሚሆን በወዳጁ በቅዱስ ሚካኤል በዓል ከሩቅና ከቅርብ ይሰብሰቡ ፡፡

4. እናንተም በምሥጋናና በጸሎት መንፈሳዊ በዓልን አድርጉ እኔ በሞትኩበት ቀን ለምሥጋና ሁሉ ጌታ የሰማይ መላእክት ደስ ብሏቸው ምሥጋና እንዳቀረቡ እንደ ዕረፍቴ ቀን ብዙ ምሥጋና አቅርቡ፡፡

7. የምመጣበትን ጊዜ እወቅ አጽሜንም በታቦቱ መንበር ፊት ሦስት ጊዜ አዙረው

8. ያን ጊዜ የጠፋው መብራት ይበራል አለው » ይላል

ምዕራፍ 62፡ 1- 8

ተክለ ሃይማኖት ከሞቱ ከ57 ዓመት በኋላ ለሕዝቅያስ አጽሜን አፍልስ ዳስስ የሚል ትዕዛዝ ለሕዝቅያስ እንደነገረው እንደ መረጃ የሚወሰደው የዮሴፍን አጽም እሥራኤላውያን ማፍለሳቸውን በመጥቀስ ነው፡፡

1. የዮሴፍ አጽም እንዲፈልስ የተናገረው ዮሴፍ በሕይወት ሳለ ለዘመዶቹ ነው፡ የፈለሰበትም ምክንያት የተባረከው ዘር አጽም በግብጽ ምድር ይቀር ዘንድ ስለሌለበት ነው እንጂ በአጽሙ እሥራኤላውያን እየተሳለሙ ታቦቱን እያዞሩ በረከት ለመቀበል አልነበረም፡፡ በመቃብርና በፈረሰ አጽም በረከት ቢኖር ኖሮ በተባረከ ዘርነት መጠሪያቸውና የሚመኩበት በአዲስ ኪዳን ለምንገኘውም በእምነት በኩል አባታችን ተብሎ የተጠራውን

የአብርሃምን የሚያህል መቃብር ሆነ አጽም ይገኝ ነበርን ? አብርሃም ታላቅ የእግዚአብሐር ወዳጅ ለእርሱና ለሚስቱ ከሰዎች መሬትን ገዝቶ እንደተቀበረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። ( ዘፍ 23: 1 - 20)

መሪያቸውና ከግብጽ የአገዛዝ ቀንበር በእግዚአብሔር እጅ ነጻ ያወጣቸው ሙሴስ ቢሆን መቃብሩን እግዚአብሔር አልሸሸገውምን ? እንዲያውም በቤተክርስቲያናችን አንዳንድ ሊቃውንት እሥራኤላውያን ሙሴን እጅግ ይወዱትና ያከብሩት ይፈሩትም ስለነበር መቃብሩን እንኳ እንዳያመልኩት ሰወረባቸው በማለት ያስተምራሉ ። ታዲያ የእኛዎቹ ይህን የአጽም ዳሰሳ በረከት ከየት ቀዱት ?

2. የፍልሰቴ ቀን የእግዚአብሔር የትንሣኤው ቀንና የወዳጁ የሚካኤል ቀን ነው የሚለው ትልቁ የገድላ ገድል ዓላማ ለእግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ መውረስ አልያም ማዘናጋት ብሎም ተደርበ ምሥጋና አምልኮ ውዳሴ መቀበል በመሆኑ እንደገድሉ ሃሳብ በርግጥ ቀኑ የጌታችንን ትንሣኤ ለማክበር የተዘጋጀ ቀን ከሆነ ሁኔታውን ባዕድ ነገር ለማስገባት የተጠቀሙበት አድርጎታል ። ይህም የሚታወቀው ጌታችን ከሞት የተነሣበት ቀን ተብሎ በተነገረለት ቀን አጽሜን በታቦቱ ፊት ሦስት ጊዜ አዙረው በማለት ዕለቱን የአጽም አምልኮን አክብሮት ቀን በማድረግ እንደለወጡት ያረጋግጣል።

ፍልሰቱን እንቀበል እንበልና የተክለ ሃይማኖት አጽም ከተቀበረ ከ57 ዓመት በኋላ በደጋፊዎቻቸው ትብብር ከነበረበት ተነስቶ ታቦቱንም ዞረ እንበልና ዛሬ አለበት ወደ ተባለበት ሥፍራ ተወስዶ ተቀበረ። የዮሴፍም አጽም ከግብጽ ወደ ቅድስት ሀገር ተወሰደ ተብሏልና።

በዮሴፍ አጽም እየተደረገ ያለ ሥርዓት ሆነ በዓል አለ ወይ ? በአብርሃም መቃብር በነቢያትም ቢሆን በታወቁ አባቶች መቃብርስ እየተደረገ ያለ ስግደት አምልኮ ዝክርና አስከሬን መሳለም አለ ወይ ? በፍጹም የለም አይደረግም። አጽም በታቦቱ ዙሪያ እንዲዞር የመደረጉ ምሥጢር ለብዙዎች ባይገባንም በመቅደስ ያለፍን ሠራተኞቹ ለነበርን ለእኛ ግን ምሥጢሩ የተገለጠ ነው ። በታቦት ላይ በአልባሳቱና በንዋየ ቅድሳቱ ሁሉ ላይ በአንዳንድ ክፉ የመቅደሱ ሠራተኞች እየተደረገ ያለው መናፍስታዊ ሥራ ሕዝቡ በመናፍስት ተጽእኖ ሥር እንዲወድቅ የሚያደርግ ሥራ እንዳለ የዓይን ምሥክሮች ነን።

ምንም እንኳ ታቦት በአዲስ ኪዳን ሥፍራ የሌለው ቢሆንም በሀገራችን ሰዎች ታቦት የእግዚአብሐርን ያህል (ለአንዳንዶችም እግዚአብሔራቸው ነው ) ስለሚፈራ የአጽሙን ማንነት በሕዝቡ አዕምሮ ለመቅረጽ የታቀደ ሰይጣናዊ ሥራ እንደሆነ ልብ ማለትን ያሻል:: ( ስለ ታቦት ወይም ጽላት በምዕራፉ ይመልከቱ )

# የተዋጀነው በተክለ ሃይማኖት ደም ነው

በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ዳግም የተወለዱ በእግዚአብሔርም ምሕረት በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት ምክንያት ውሉደ እግዚአብሔር የተባሉ ክርስቲያኖች ስለመዋጀታቸው ሲያስቡ « የክርስቶስ ደም » ተስፋቸውና አለኝታቸው ነው::

ሐዋርያትም « በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያን» በማለት ቤተክርስቲያን ( የምዕመናን አንድነት ) በሌላ በማንም ሳይሆን በእግዚአብሔር ልጅ ደም የተዋጀች እንደሆነች አስረግጠው አስተምረዋል:: ስመ ጥር ቅዱስ ጴጥሮስም «የተዋጃችሁት የአሪት ሰዎች ይጠቀሙበት እንደነበረው በበጎችና በፍየሎች በኮርማዎችም ደም አይደለም በክቡር የክርስቶስ ደም እንጂ» በማለት የምዕመናንን የመዋጀት ሥራ ለክርስቶስ ደም ሰጥቶ ይናገራል::(1ኛ ጴጥ 1:18-19 )

ደጋግ አባቶቻችንን « ቤተክርስቲያንን በክቡር ደምህ ትቀድሳት (ታነጻት) ዘንድ በጥፊ ተመታህ (የምድኃኔዓለም ዋዜማ የመጋቢት ) በማለት በተናገሩባት ቤተክርስቲያን « በገድሉ ደም (ተክለ ሃይማኖት ማለታቸው ነው ) የዋጀንን ኃጢአቶቻችንን የሚያቀልልን» ይህ ተክለ ሃይማኖትን እግዚአብሔር ሰጠን በማለት ድርሰት ጽፈው ሕዝቡን ለኃጢአት ሥርዩቱ ክርስቶስን ሳይሆን ተክለ ሃይማኖት የተባሉትን ሰው እንዲማጸን አድርገዋል::

የሕዝብን ኃጢአት ለማስተስረይ ... የሚምርና የታመነ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ነው እያለ መጽሐፍ ቅዱሳችን ( ዕብ 2:17 1ኛ ዮሐ 2: 2 ) ደራሴ ገድለ ተክለሃይማኖት ደግሞ መዋጀታችንና ደኅንነታችን በፍጡር ሰው ደም ነው በማለት ክኅደትን ይሰብካሉ:: የታወቁትን ቅዱሳን አባቶች ትምህርት የያዘው

ሃይማኖተ አበው የተባለው መጽሐፋችን ስለ ደጎንነታችንና ስለመዋጀታችን ሲናገር «ደኅንነታችን በዕሩቅ ብእሲ ( በፍጡር ሰው ) አይደለም ፡ ይልና በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሽ የሆነ ፍጡርን የሚደገፍ ቢኖር ርጉም ይሁን በሚለው ውግዘት ደምድሟል። ጸሐፊዎቹ ግን ይህን የአባቶች ውግዘት በማለፍ የክርስቶስን ውለታ ለማስረሳት የተዋጀነው በተክለ ሃማኖት ደም ነው ብለዋል። በኤፌ 1፡ 7 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር « ለክብር ወለስብሐት በጸጋሁ ዘጸገወነ በወልዱ ፍቁሩ ዘበእንቲአሁ ረከብነ መድኃኒተ ወተኀድገ ኃጢአትነ በደሙ በከመ ብእለ ጸጋሁ » ትርጉም « በውድ ልጁም እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ሥርየት ነው » ብሏል።

ጸሐፊዎቹ ግን ሕዝቡን ለማደናገር « በገድሉ ደም የዋጀንን ይህን አባታችንን (ተክለ ሃይማኖትን ) አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሰጡን ብለዋል። ሐዋርያት ግን ይህን አላስተማሩም ። ቅዱስ ጳውሎስ « ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ወደ ዓለም መጣ የሚለውን ቃል ሁሉም ሊቀበሉት የሚገባና የታመነ ነው » ሲል ቅዱስ ጴጥሮስም ደግሞ «እኛም አይተናል አብ የዓለም መድኃኒት እንዲሆን ወደ ዓለም እንደላከው» ብሏል ። « የምንድንበት ሌላ ስም ከሰማይ በታች የለም እንዳልተባለ ሁሉ ጸሐፊ ድርሳናት ወገድላት ተሆኑት አገር በቀል መናፍቃኑ ግን በተክለ ሃይማኖት ደም እንድንዋጅ የሰጠን እግዚአብሔር ነው በማለት ለወንጀላቸው ተባባሪነት እግዚአብሔርን ጠርተዋል።

በቅዳሴያችን ላይ እንኳንስ የተክለ ሃይማኖት ቀርቶ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የሞቱ ሰዎች ደም እንዳልጠቀመን እንዲህ የሚል ቃል አለ ።

«ወሶበ ርእየ እግዚአብሔር ከመ ኢበቁአ ለአድኅኖ ዓለም ደመ ነቢያት ቅዱሳን እምደመ አቤል ጻድቅ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ፈነወ ለነ ወልዶ መድኅነ ወመቤዝወ »

ትርጉም

« ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የፈሰሰው የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እንዳልበቃ ( እንዳልጠቀመ ) ባየ ጊዜ እግዚአብሔር መድኃኒትና ቤዛ የሆነውን አንድያ ልጁን ላከልን » ብሏል። ( ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ)

# ምዕራፍ ሦስት

# ገብረ መንፈስ ቅዱስ

እንዳልነው የገድሉ ምንጮች የሆኑት መናፍቃን ያገኙትን ሰው ስም ደስ ካላቸው ያጸድቃል፣ እንደ መላእክት ወይም እንደ እግዚአብሔርም ፍጹም የሆነ፣ ሲያሻቸው በአየር ላይ የሚሄድ፣ ለዘላላም እህል ሳይቀምስ የኖረ ፣ እንደ ሰው ያልሆነ ልዩ ፍጡር እያደረጉ ስለሚደርሱ እነርሱ ጻድቅ ያሉትን ሁሉ ተሰፍሮ የማያልቅ ታይቶም የማይታወቅ ብቃትና ችሎታ ሥልጣንና ኃይል እስካፍንጫው ያስታጥቁታል::

የዚህ ገድል ደራሲም በመጀመሪያ የአንባቢዎቹን ኅሊና ለመያዝ ስለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ በማለት ገጸ ባሕርዩን ይስለዋል:: ከግብጽ ምድር የመጣ ( እስክንድርያ እናቱ ማርቆስ አባቱ እያለ ሲጠራ ለኖረ ሕዝብ ከግብጽ እስክንድርያ በረከት መጣልህ ሲሉት እንዴት እንደሚቀበላቸው ያውቃሉና ) በግብጽ በረኃ 300 ዓመት የኖረ ( ለዚህ መረጃቸው እግዚአብሔር ምን ይሳነዋል ) በዝቋላ ገዳም እህል ሳይበላና ሳይጠጣ ልብስ ሳይለብስ 262 ዓመት የኖረ እንደ መላእክት እንጂ እንደ ሰው ያልተመላለሰ ( ምዕ 1÷ 1-2 ) መልአኩ ገብርኤል መጥቶ በእናቱ ማሕጸን ሳለ ስም ያወጣለት ( እንደ ኢየሱስ) በተወለደ ዕለት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ሦስት ጊዜ ሰግዶ ያመሰገነ ( የአንድ ቀን ልጅ) መልአክ በሦስት ዓመቱ ወስዶ ገዳም ያስገባው ( ለምን ? ) እስከ ሰባቱ ሰማይ የተወሰደ በዚያም እግዚአብሔር የባረከው ከአዳም ጀምሮ ያሉ ሰዎች ሄሮድስ እስካስገደላቸው ያሉ ሕጻናት በመፈራረቅ የባረኩት፣በመጨረሻም የማሳረጊያውን ባርኮት ድንግል ማርያም ያደረገችለት ( 2: 1- 11) አንበሶችና ነብሮች የሚታዘዙት የሚላኩለት ( 60 አንበሶችና 60 ነብሮች ) ከራስ ጸጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ ጸጉር የሞላበት ( በሰውነቱ ላይ ያለው ጸጉር ቁመቱ 1 ክንድ ከስንዝር ነው ይላል ) ዓይነት ሰው ነበር በማለት የአንባቢዎቹን ቀልብ ምናባዊ በሚባለው የድርሰት ዓይነትና ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ባልታየ ገጸ ባሕርይ አገላለጥ ለማንበርከክ ታግሏል:: በነገራችን ላይ ከግብጽ መጡ የሚባሉት ገ/መ/ቅዱስ በግብጽ ቤተክርስቲያን ታሪክ የሌሉና በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ( እስክንድርያ ) በቅዱስነት ያልተቀበለቻቸው ሰው እንደሆኑ

የታሪክ ተመራማሪዎችና እስክንድርያ ሄደው ቤተክርስቲያኒቱን ጠይቀው የመጡ የራሳችን መምህራን በግልጽ ይናገራሉ ::

በሰፊው በመድረክ ላይ እንደተለመደው ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተወለዱ የተባለበት ቀን የጾም ቀን ስለነበር እናታቸው ጡቷን ስትሰጣቸው « ምን አልሁሽ በጾም ቀን? » በማለት እናታቸውን እንደገሰጹ ይነገርላቸዋል። መንፈሳዊነት ሽክም ክርስትና ዕዳ ለሆነበት መጽደቅ ፈጽሞ የማይቻል መስሎ ለሚታየው የቤተክርስቲያናችን ምዕመን በተወለዱ በመጀመሪያው ቀን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምሥጋና አቀረቡ፣ በጾምም የእናት ጡት አልጠባም አሉ በሦስት ዓመታቸውም መልአክ ገዳም ወሰዳቸው ተብሎ የተነገረለትን ሰው በእግዚአብሔር ፋንታ ለማድረግ እንደሚቃጣው ያገጠጠ ልማዳችንና ታሪካችን ያጋልጠናል።

በቦሪዳ መላእክት ሲቀድሱ ሰማሁ ያላቸውን አንድ ግለሰብ በመስማት ታላላቅ የሃይማኖት አባቶች ሳይቀሩ እንደተታለሉ ቅዱስ ብለው እንዳስተዋወቁት እመቤታችን የላከችው መልክተኛ ተብሎም በየመጽሐፉ እንደተወደሰ በዚህም ስብከት ያታለለው ሕዝባችን የመላእክትንም ቅዳሴ ለመስማት ለዓመታት ይጎርፍ እንደነበር ዛሬ ግን ይወርዳል ተብሎ የነበረው በረከት ሆነ ቅዱሱ ሰው ደብዛቸው እንደጠፋ ማስታወስ በቂ ነው። ( ሐመር መጽሔት ተመልከት )

እመቤታችን የላከቻቸው ተብሎ ስፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ይከተላቸው የነበሩት የቅርቡ ባሕታዊም በረከት ለመቀበል የጎረፈው ሕዝብ ፍሬ አልባ በሆነው ትምህርትና ሕይወታቸው ጥሏቸው እስከ ሄደ ድረስ ክርስቶስን አምኖና በክርስቶስ ጸጋ ኖሮ መጽደቅ ያልለመደው ሕዝባችን የሚናፍቀውን ጽድቅ ሆነ የዘላለም ሕይወት ለማግኘት እንዴት ይኳትን እንደነበር ከምስል ጋር የተደገፈ መረጃ በእጃችን አለ ::

በእግዚአብሔር ስም እየተሸፈኑ ተልከናል በማለት ለሚነሱ ሁሉ በቀላሉ የሚታለለው ሕዝባችን በገድሉ ጸሐፊዎችም ኢላማ ገብቶላቸው ለዘመናት ሲያጃጅሉት እንደኖሩ በእግዚአብሔር ጸጋ ደፍረው በተነሱ ወገኖች : ጉዳቸው እየታየ ያሉት መጻሕፍት ራሳቸው ይመሰክራሉ።

እንዲህ አድርገው የፈለጉትን ሰው ከሳሉ በኋላ የዚህን ሰው ስም የጠራ መታሰቢያውን የሚያደርግ ኃጢአተኛ ሁሉ ኃጢአቱ ተምሮ ርስተ መንግሥተ ሰማያት እንዲገባ እግዚአብሔር ቃል ገብቶለታል ይሉታል።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ የእግዚአብሔር ጽድቅና ምህረት ስለማይገባን ማገኛውም ሰው ፣ በክርስቶስ ምክንያት « ጸድቄአለሁ » ማለት ድፍረትና ኃጢአት ይመስለዋል:: በምትኩ « ኃጢአተኛ ነኝ ቦታየም ሲኦል ነው » ብሎ መናገር ትሕትና ተደርጎ ስለሚቆጠር ዘር ማንዘራችን ጽድቅንና የጽድቅን ነገር ሳይማሩ ያልፋሉ አልፈዋልም:: እንዲያውም የመቅደስ ሠራተኞችን ጨምሮ « ሲኦልን እንኳ በቅጡ በሰጠኝ » በሚል ስላቅ ተስፋቸውን ገድለው ያልፋሉ::

ይህን ያጤኑ መናፍቃኑ ደራሲዎች « ዕገሌ የሚባል ጻድቅን ስም የጠራ ዝክሩን የዘከረ ጥላ ከለላ ሆነው እንዲያጸድቁን እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶላቸዋል: ስለዚህ በከንቱ ላይሆንልህ ከምትደክም የጻድቁን ዝክር ብቻ አድርግ በማለት በዚህ ጽሑፍ ዘርዝረን የማንጨርሰውን ሰውና መላእክት የዝክር ቃል ኪዳን ይደረድራሉ::

በዚህ በገድለ ገብረ መንፈስ ቅዱስም የሚሉት ይህንኑ ነው:: ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስሙን ለሚጠሩ ብቻ ሳይሆን ቃል ኪዳኑ ሲፈልግ ወደ ሲኦል ሄዶ ሰው ማውጣትና ማጽደቅ የሚያስችል ጸጋ እንዳለው ገልጸዋል::

በእውነተኛው መጽሐፍ ቅዱስ ጌታችን መድኃኒታችን ሲናገር « በሲኦል የነበረውን ባለጠጋና ከአብርሃም ጋር በአብርሃም እቅፍ ስለነበረው ድኃ ሰው በምሳሌ እንዲህ አለ:: በሲኦል የነበረው ባለጠጋ ሰው ከመከራው ጽናት የተነሳ አንተ ጋ ያለው ሰው ጣቱን በውኃ ነክሮ ጉሮሮየን ያረጥብልኝ ዘንድ ላክልኝ በማለት አብርሃምን ሲናገረው፣ አብርሃም ጻድቁ «በእኛና በእናንተ መካከል ትልቅ ገደል አለ » በማለት ከሲኦል እነርሱ ወደእሱበት ፍልሰት እንደሌለ አስረግጦ ተናግሮታል::

በንግግራቸው ውስጥ ሰውየው የተጸጸተ ይመስላል:: እንዲያውም በምድር ወደሚገኙ ሰዎቹ ከመንግሥተ ሰማያት ሰው ተልኮ ንስሐ እንዲገቡና እንዲድኑ አብርሃምን ሲጠይቀው አሁንም ለጽድቅ ከሰማይ ሰው ወርዶ መስበክ የተከለከለ ነው በማለት መልሷል:: እነ መንገደ ብዙ ግን « ጌታችን የመላእክት አለቆችን እንዲህ አላቸው ስለ ወዳጄ ስለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ምልጃ ወደ ገሃነም ሂዱና የኃጥአንን ነፍስ አውጡ ከእሥራታቸውም ፍቱአቸው ብሎ ተናገረ » ሲቃነ መላእክቱም ሄደው ከሲኦል ነፍሳትን አውጥተው ወደ ገነት አስገቧቸው በማለት ከሲኦል እንኳ ቢሆን በገብረ መንፈስ ቅዱስ የታመነች ኃጢአተኛ ነፍስ እንደምትወጣ አጉል ተስፋን በመናገር ሕዝቡን ከክርስቶስ ጸጋ ለይተውታል::

ወንጌላዊው ዮሐንስ « በልጁ የሚያምን አይፈረድበትም የማያምን ግን አሁን ተፈርዶበታል »ምክንያቱም አሁን በልጁ አላመነምና ነው ይላል ። በልጁ የሚያምን ግን ቦታው ርስተ መንግሥተ ሰማያት መሆኑ የታመነ ነው ።ባለማመን የኖሩ ግን ቦታቸው ሲኦል ብሎም ገሃነመ እሳት ነው። እነዚህ ሰዎች እድላቸው በሕይወት እስካሉ ድረስ ብቻ ነው እርሱም በክርስቶስ በማመን የሚገኘውን የዘላለም ሕይወት ያገኙ እንደሆነ ብቻ ነው። ሆኖም ወደ ሲኦል ከገቡ በኃላ ወይም በክርስቶስ በማመን ዳግም ሳይወለዱ ቀርተው ቢሞቱ በየትኛውም መጽሐፍ ሌላ በሲኦል የሚደረግ ንስሐም ሆነ አመክሮ እንደሌለ ከንቱ የሆነው የራሳችን የግንዘት መጽሐፍ እንዲህ ይላል « እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ንስሐ » ትርጉም « ሰው ከሞተ በኋላ ንስሐ የለውም » ( መጽሐፈ ግንዘት )

የዚህ ኢ. አማኒ ነፍስ በሥጋ ሳለችም ተፈርዶባታል ይላል ከሥጋ ስትለይም እንዲሁ ትሄዳለች እንደተፈረደባትም ትወርዳለች ። ታዲያ ቅዱሳን እያልን የሰየምናቸው ሰዎች ቃል ኪዳን ይሆን የጌታ ቃል የሚጥስ ነውን ? ። ወይስ የሲኦል አጋፋሪ ናቸውን ?

የዚህ ገድል እኅት የሆነው ገድለ ክርስቶስ ሠምራ የሚባለው መጽሐፍም በክርስቶስ በማመን ጽድቅን ከመስበክ ይልቅ ሰው ሲኦል ከገባ በኋላ በቅዱሳን ቃል ኪዳን መውጣት እንደሚቻል በማበረታታት ይናገራል። ጻድቅት ክርስቶስ ሠምራ ከፈጣሪዋ በተሰጣት ቃል ኪዳን መሠረት በየቀኑ ከሲኦል 3000 ነፍሳት ታወጣለች ይላል።

ለሰሚው ግራ የሆነው ይኸው ገድል አንድ ቀን ክርስቶስ ሰምራ ሳጥናኤልንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ እግዚአብሔርን ታረቅልኝ አለችው ይላል። እግዚአብሔርም እሺ አይልሽም እንጂ ሂጂ ሞክሪ ብሎ ላካት ይላል። ባሕርዩ ከማይስማማው ከሰይጣን ጋር ቅዱሱን እግዚአብሔርን ለማስታረቅ ሙከራ አድርጋለች የተባለችው ሴት ጤናማ ናት ብሎ ለመቀበል የሚከብድ ሲሆን ከሁሉ የሚገርመው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሠምራ አስታራቂነት ከጠላቱ ከሰይጣን ጋር ታርቆ በሰላም ለመኖር እሺ ካለሽ ሂጂ ብሎ ተስማማ ማለት በእግዚአብሔር ቅድስና ላይ እንደመቀለድ ይቆጠራል።

ለእግዚአብሔር አማካሪውስ ማን ነው ? እርሱንና ሰይጣንን ለማስታረቅ ከእግዚአብሔር የተሻለ አስተሳሰብ ያለው ማን ነው ? እንዲታረቁስ

እግዚአብሔር ሽማግሌ እየፈለገ ነውን ? ይህን ወንጀል ነው እንግዲህ ሰው እንዲሳለመው እንዲያከብረው ሌትና ቀን የሚሰበከው ::

ክርስቶስ ሠምራም ወደ ሲኦል ሄዳ « ሳጥናኤል» ብላ ጠራችው ይላል ገድሉ ሰይጣንም « ማን ነው በድሮ ስሜ የሚጠራኝ » ብሎ ተገረመ :: ከሲኦል ወጥቶም እጇን ይዞ የኃጥአን ነፍስ ባሉበት መጨረሻ ላይ ጣላት፡ እግዚአብሔርም ሚካኤልን ጠርቶ ፍጠንና ሂድ ክርስቶስ ሠምራ ወዳጄን አስጥላት ብሎ ላከው፡ ሚካኤልም ሄዶ ባጣት ጊዜ የት እንደደበቃት ለመፈለግ እንዲያመቸው በሲኦል የነበሩትን ነፍሳት አንድ በአንድ እያወጣ ከጨረሰ በኋላ የክርስቶስ ሠምራን ነፍስ አገኘና ይዟት ሄደ :: እነዚያ በምክንያተ ክርስቶስ ሠምራ ወጥተው የነበሩት ነፍሳት ገነት መንግሥተ ሰማያት ገቡ በማለት ተርኳል:: ሚካኤል ሺህ በክንፉ ሺህ ባክናፉ ይሉታል ሲያሞካሹት::

መቼም ደራሲዎቹ ጤንነት የጎደላቸው በሽተኞች ናቸው እየተባሉ ከወንጀላቸው እንደሚያመልጡ ጥፋተኞች ወንጀላቸውን ማቅለል ተባባሪ የመሆን ያህል ነው :: ይህን ያህል ልብ ወለድ ድርሰት ጽፈው ከመቸገር እንደ ሐዋርያቱና ደጋግ አበው በክርስቶስ በማመን ጽድቅ እንዳለ መስበኩ ጠፍቷቸውም አይደለም :: ሆን ብለው የተነሱበት ዓላማና ግብ ያላቸው ሰውን ወደ ሞት ለመንዳት የተፋጠኑ ነፍሰ ገዳዮች ናቸው እንላለን::

## ጣዖት አምላኪው
## በገ/መንፈስ ቅዱስ ተአምር ገነት ገባ

በማያሻማና በማያደናግር ገለጣ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም አለ:: ( ዮሐ 14 ÷ 16) ይህን አልተረዳንም ወይም ትርጉሙ ሌላ ይሆናል ለሚሉ ደግሞ ምርጥ ዕቃ ጳውሎስ « በእርሱ ( በክርስቶስ ) በኩል የሚመጡትን እግዚአብሔር ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል:: ( ዕብ 7 ÷ 25)

በማለት ለእነ አንድምታ ብዙ የአንድምታ ማምለጫቸውን በአጭር ትርጉም ያሳጥርባቸዋል።

«ምንተ እግበር ከመ እድኃን » ትርጉም «እድን ዘንድ ምን ላድርግ » የሐዋ 16 ÷ 31 ) ሲላቸውም «እመን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወተሐዩ አንተ ወኵሉ ቤትከ » ማለትም « በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ » እያለ ሰው ይጸድቅበት ዘንድ ያለውን መንገድ ያስረዳል።

ሰቃልያን እየተባሉ የሚጠሩት የአይሁድ ካህናት ስለ ኃጢአት ሥርዬት የሚያውቁትና የሚረዱት እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ስለነበር በሥጋ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ልጅ ኢየሱስን አንተ እንዴት የኃጢአትን ስርዬት እሰጣለሁ ትላለህ ሲሉ « ከአንዱ ከእግዚአብሔር በስተቀር ኃጢአትን ማን ሊያስተሰርይ ይችላል ? በማለት ሲጠይቁትና ሲያጉረመርሙ ነበር ። ( ) ችግራቸው እግዚአብሔር ኃጢአትን ለማስተስረይ የፈቀደበትን ጥበብና መንገድ ያለመገንዘባቸው ነበረ እንጂ ኃጢአት በእግዚአብሔር እንጂ በሰው ነው አላሉም።

እግዚአብሔር በፊት የተሠራ ኃጢአትን ለመተው ያለውን ችሎታና ፈቃድ ሲያሳይ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ አለ። ሮሜ 3: 24 ) አብ ለምን ይህን መንገድ እንደመረጠ ከእኛ አስተያየት ይልቅ የእርሱ መለኮታዊ እውቀትና ፈቃድ ስለሚበልጥ እርሱ የሚጠቅመንን አደረገ እንላለን።

እንግዲህ የዘላለም ሕይወት ( ጽድቅ ) እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ውሳኔ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት በእርሱም በኩል በሆነ እምነት የሚገኝ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ማንም እድን ዘንድ ምን ላድርግ ቢል ሐዋርያት አባቶቻችን እንዳሉት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ከማለት ውጪ ሌላ የለንም።

የእኛዎቹ የገድል ባለሙያዎች ግን ይህን በጎ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሐዋርትንም ትምህርት በመቃረን ስለ ዘላለም ሕይወት ሲጽፉ እንዲህ ብለዋል

፩. ተአምሪሁ ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለሰሚዐ ዕጹብ ወለርእይ መድምም ወሀሎ አሐዱ ብእሲ ኃጥእ ወይገብር ብዙኃ ሥራያተ ጣዖት ወአማልክተ ወዝሙተ ብዙኃ::

፩፥ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ተአምር ለማየት ለመስማት ዕጹብ ድንቅ ነው አንድ ኃጢአተኛ ሰው ነበር ብዙ ሥራይ የሚያደርግ ጣኦትን በማምለክ ምሥልን በመሥራት በማመንዘር ብዙ ኃጢአት ይሠራ ነበር::

፪. ወአሐተ ዕለተ ሖረ ኀበ ሀሎ መጽሐፈ ገድሉ ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አመ ፭ ለመጋቢት ወሰምዐ እንዘ ይትነበብ መጽሐፈ ገድሉ ወኪዳኑ ለአቡነ ዘከመ ወሀቦ እግዚእ ኪዳነ ምሕረት ለሰብእ እለ ይገብሩ ተዝካሮ::

፪፥ አንድ ቀንም የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ገድል የሚናገር መጽሐፍ ወደ አለበት በመጋቢት አምስት ቀን ሔደ ገድሉን ኪዳኑን የሚናገር መጽሐፍ ሲነበብ የጻድቁን መታሰቢያ ለሚያ ደርጉ የሰጠውን የምሕረት ኪዳን እንደሰጠው ሰማ::

፫.ወእምዝ ኀለየ በልቡ ወበኀሊናሁ ውእቱ ብእሲ እንዘ ይብል እምይእዜሰ እገብር ተዝካሮ ወእትአመን በጸሎቱ::

፫. ከዚህ በኋላ ያ ከእንግዲህስ ወዲህ የጻድቁን መታሰቢያ አደርጋለሁ በጸሎቱም እታመናለሁ ብሎ አሰበ::

፬.ወከመዝ ሰሚዖ መጽሐፈ ገድሉ ለአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወፅአ ወሖረ እምህየ ወረከብዎ ጸናሕያነ ፍኖት ወዘበጥዎ ዐቢየ ዝብጠተ ወነሥኡ አልባሲሁ ወሰለብዎ::

፬. እንደዚሁ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን የገድሉን መጽሐፍ ሰምቶ ከዚያ ወጥቶ ሲሄድ በመንገድ ያሸመቁ ወንበዴዎች አግኝ ተው ጽኑ ድብደባ ደበደቡት ልብሱንም ገፈው ወሰዱበት::

፭. ወእምዝ ገብአ ውስተ ቤቱ እንዘ ጥሙቅ በደም ወበይእቲ ዕለት ሞተ ወመጽኡ መላእክት ወወ ሰድዋ ለነፍሱ ኀበ መንበሩ ለእግዚአብሔር ወአቀምዋ

፭. ከዚህ በኋላ በደም ተነክሮ ወደ ቤቱ ገባ በዚያች ቀንም ሞተ መላእክትም መጥተው ነፍሱን ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ፊት ወስደው አቆሟት::

ቅድማሁ::

| | |
|---|---|
| ፲. ወበጊዜሃ መጽአ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወቆመ ቅድመ እግዚአብሔር ወይቤ መሐር ሊተ ዛተ ነፍስ እስመ ተአመነት በምሕረትከ ዘገበርከ ሊተ ወበኪዳን ዘወሀብከኒ:: | ፲፥ ያን ጊዜም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በእግዚአብሔር ፊት በአደረ ግኸው ቸርነትና በሰጠኸው ቃል ኪዳን አምናለችና ይህችን ነፍስ ማርልኝ:: |
| ፲. ወይቤ እግዚእነ ሰረይኩ ላቲ ኃጢአታ በእንተ ገብርየ ወበእንተ ቃልየ ዘኢይትኄሰው ሰድዋ ኀበ ማኅበረ መሐይምናን:: | ፲. ጌታችንም ስለ አገልጋዬ ስለማይታበል ቃሌም ኃጢአቷን ይቅር ብያታለሁ ወደ መሃይምናን አንድነት ውሰዷት አለ:: |
| ፳. ወአዘዞ ለቅዱስ ሚካኤል ከመይሰዳ ውስተ ሕይወት ዘለዓለም ወተፈሥሐ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ወበርሀ ገጹ ከመ ፀሐይ:: | ፳. ቅዱስ ሚካኤልን ወደ ዘለዓለም ሕይወት እንዲ ወስዳት በአዘዘው ጊዜ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ደስ አለው ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ:: |
| ፱. ጸሎቱ ወበረከቱ የሀሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን:: | ፱. ጸሎቱ ለመናጦ ይደረግልን በረከቱ ይደርብን ለዘላለሙ አሜን:: |

ክርስትና ስለ መንግሥተ ሰማያት የሚያስተምረው ደግሞ ሰው በሕይወተ ሥጋ እያለ የወንጌልን ቃል ሰምቶ ሲያምንና ንስሐ ሲገባ ያ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል ይላል ( ሮሜ 4÷ 1-4 እንዲሁም « አምናችሁ ትድኑ ዘንድ ( ዮሐ 21÷ 21 ) ሲል ይህም እምነት በሌላ በማንም በኩል ሳይሆን በእርሱ (በክርስቶስ ) የሚያምን ( ዮሐ 3÷ 16 )ነው ተባለ:: ጌታችንም በእኔ የሚያምን እንዳለ ( ዮሐ 6÷ 48 )

ጸሐፊዎቻችን ግን ይህን ወደ ጎን በመተው ሰው በሕይወት ዘመኑ ቃሉን ሰምቶና በቃሉ ኖሮ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ሥራ ታምኖ ከዚህ ዓለም ጥፋት እንዳይድን በፈለገው ኃጢአት እየበለጠገ ቢኖርም በቅዱሳን ቃል ኪዳን

ከሞት በኋላ እንኳ ቢሆን ከሲኦል ወደ መንግሥተ ሰማያት መመለስ የምንችልበት አሠራር አለን በማለት የድፍረት ኃጢአትን ይናገራሉ::

በገድሉ ላይ ሰውየው የሞተው በኃጢአተኛ ሕይወቱ ነው ይላል ያውም ጣዖት አምላኪ :: ገብረ መንፈስ ቅዱስ ይህን ሰው የሚያውቁበት ነገርና በታ ነበራቸው:: « ተገኘራቸውን እየደገሰ ገ/መ/ቅዱስን ለማክበር እንደወሰነ ( ቁርጥ ኃሳብ እንዳደረገ ) ሰውየውም በእግዚአብሔር ፊት ፊጥነው በመድረስ እግዚአብሔርን ይህች ነፍስ ትማርልኝ በማለት ጠየቁ በአማላጅነታቸውም አስምረው መንግሥተ ሰማይ እንዳስገቡት ተነግሯል::

እንዲህ ከሆነ ደግሞ :-

1. እግዚአብሔር ዓለም በልጁ እንዲድን ያለውን ቃል ጌታችን አፍርሶታል ማለት ነው:: ( ገ/መ/ቅዱስ በቃል ኪዳኔ ታምናለችና ሲሉት እሺ ብሏቸዋልና )
2. በክርስቶስ ያላመነ አሁን ተፈርዶበታል የሚለው የጌታ ቃል በራሱ በጌታ ተሽሯል ማለት ነው ( በጌታ ሳያምን የሞተን ሰው አጽድቋልና
3. መጽሐፍ በቅዱሳን መኖሪያና በኃጥአን መኖሪያ መካከል « ትልቅ ገደል » ተመስሎየተነገረው ልዩነት ተሻረ ማለት ነው ( ገ/መ/ቅዱስ ከሲኦል አውጥተው ወደ ገነት ለማስገባት ችለዋልና )
4. አብ በክርስቶስ በኩል የሚመጡትን ሊያድናቸው ይችላል የተባለውም ፈረሰ ( በገ/መ/ቅዱስ በኩል መግባት ይቻላል ብለዋልና

በዚህ በገብረ መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ደግሞ የተገለጠውና ኃጢአተኛ ነበረ የተባለው ሰው የገድሉን መጽሐፍ ( ተረቱን ) ሲሰማ ወሰነ የተባለው « የገብረ መንፈስ ቅዱስን መታሰቢያ አደርጋለሁ አለ» ነው የሚለው :: ቅዱስ መጽሐፍ ደግሞ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ሲያምን ውሳኔው « ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ሊያድን መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉም ሊቀበሉት የተገባ ነው ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ ስለዚህ ግን የዘላለም ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ምሳሌ እሆን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግሥቱን ያሳይ ዘንድ ምህረትን አገኘሁ » ይላል:: ( 1ኛ ጢሞ1÷ 15- 16 )

የተከበራችሁ አንባብያን በሁለቱ ኃጢአተኞች መካከል የተወሰነውን የውሳኔ አይነት ስንመለከት የሰማይና የምድርን ያሕል ልዩነት ይታይባቸዋል

ሟርተኞች ጣዖት አምላኪዎች ፣ አመንዝሮች ፣ሌቦችና ቀማኞች ከአሉበት እሥራት ወጥተው የዘላለም ሕይወት ያገኙ ዘንድ የገብረ መንፈስ ቅዱስን ዝክር መደገስ ሳይሆን እግዚአብሔር የዓለም መድኃኒት አድረጎ በላከው በልጁ ማመን ብቻ በቂ እንደሆነ መጻሕፍት ይተባበሩበታል ። ጽድቅ በክርስቶስ ሆነ እንደተባለው ነዋ። ( 1ኛ ቆሮ 1÷ 31 )

# ተአምረ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ጽንስ አስወረደ

ገድላትና ድርሳናትን እየከተቡ የሚያከፋፍሉን እነዚህ መናፍቃን በእግዚአብሔር ዘንድ እንኳ የተከለከለውን ነገር እነርሱ ጽድቅና የሚከናወን በጎ ተግባር በማድረግ ሕዝቡንም በዚህ የክፋት ሥራቸው በማስተባበር በፍርድ ሥር እንዲወድቅ ያደርጉታል።

በዓለማችን ያሉ ስለ ሰብአዊ መብትና ስለ እንስሳት ሕይወት ተሟጋች የሚባሉ ድርጅቶች ሆኑ ሰብአዊ ርኅራኄ አላቸው የሚባሉ አንዳንድ ታዋቂ ግለሰቦች ምንም እንካ በክርስቶስ በማመን ሐዲስ ተፈጥሮ ባይሆኑም ባላቸው ሰብአዊ እውቀትና ቸርነት ጽንስ ማስወረድ የሰውን መብት መግፈፍ ነው በማለት በዓለም ላይ የሚደረጉ የጽንስ ውርጃ ሕጋዊ መሆን የሚከራከሩትንና ደጋፊዎች በመቃወም የጽንስ ማስወረድን ሕጋዊነት በዓለም እንዳይጸድቅ ይሟገታሉ ።

በተለይም ቤተክርስቲያን በምንም ምክንያት ቢሆን ጽንስ ማስወረድ በእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ተቃውሞ ማድረግ ስለሆነ ከምድራዊ ወንጀልነቱ አልፎ በመንፈሳዊው ቋንቋ ኃጢአትና በእግዚአብሔር ፊት የሚያስጠይቅ ነፍስ ገዳይነት በመሆኑ ቁጥር አንድ የጽንስ አስወራጅ ድርጅትን ሆነ መንግሥትን በመቃወም የምትቆም የእግዚአብሔር አምባሳደር ናት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የተባለውን ሰው ቅድስና አበዛን ላላቅን የሚሉት ጸሐፊዎች ይህን በሚጋፋና በሚቃረን መልኩ እንደ እነርሱ አባባል ጻድቁ ጽንስ በማስወረድ ረገድ እንደተባበሩ እንዲህ ጽፈዋል።

አንዲት ሴት በዝሙት ምክንያት መጽነሷ በሊቀ ደብሩ ( የደብሩ አለቃ ) ተሰማ። ሊቀ ደብሩም ወደመምህሩ አሰማ መምህሩም ቁጡና ኃይለኛ ሰው ስለነበሩ መልእክቱ በተነገራቸው በ3ኛው ቀን እንደሚመጡና ነገሩን እንደሚያጣሩ መልእክት ላኩ። ይህንንም የመምህሩን ውሳኔ በዝሙት የጸነሰችው ሴት ሰማች።

ሴቲቱም እያለቀሰች የገብረ መንፈስ ቅዱስ ገድል ነው የተባለውን መጽሐፍ ቁሱን ስጠኝ አለችና እየተሳለመች ወደ ልብሷ ውስጥ አስገባችው ስትጸልይም ከዚህ ኃዘኔ ብታጽናናኝ ከዚህ ቁጡ ሰው ብትሰውረኝ እጅ መንሻህን ውሰድ ብላ ለቄሱ ዕጣን ሊያጥንበት ሰጠችው። አቡነ ገ/መ/ቅዱስ ሆይ እንዲህ አድርገህ ብታጽናናኝ የሠራሁትን ኃጢአት ብትሰውርልኝ እኔም ባርያህ እሆናለሁ በማለት ተናገረች። ይላል።

ገብረ መንፈስ ቅዱስም ወደፈጣሪው ቀርቦ አማለዳት ያን ጊዜ በገ/መ/ቅ ጸሎት በሆዷ የነበረው ጽንስ ጠፋ በማለት የጻድቁን ገድል ይሁን ወንጀል ይተርካል።

አትግደል የሚለው ሕግ ለእነርሱ ተረት ተረት ነው ። አንድ ነገር ሊታወቅ የሚገባው ቢኖር እግዚአብሔር የኃጢአተኛን መጥፋት ባይወድም ኃጢአትን ግን በመተባበር አይሠራም በዝሙት ልጅ የወለደውንና እንደ ልቤ ያለውን ዳዊት፣ እንዴት እንደቀጣው በግልጽ ተጽፎ እያለ እግዚአብሔር በገ/መ/ቅ አማላጅነት ጽንስ በማስወረድ ይተባበር ነበር በማለት መጻፍ ድፍረት አይሆንምን ?

ይህን ያለ ክርስቶስ እየኖረና መላ ሕይወቱ በተሰወረና በተገለጠው ኃጢአት ተይዞ እየተሰቃየ ያለው ሕዝባችን ኃጢአተኛ መሆኑ እየተሰማው ከዚህ ይገላገል ዘንድ ከሀገር ሀገር ከደብር ደብር ከገዳም ገዳም እየተዘዋወረ፡ አቡየ አድኑኝ፣ ተክልየ ጠብቁኝ፣ እመ ብርሃን አንቺ ታውቂያለሽ እያለ በመማጸን ግን ኃጢአተኛነቱ ፈጽሞ የተፋቀለት ለመሆኑ ማረጋገጫ አጥቶ ከታቦት ታቦት እጣ እየጣለ ይህኛው ቶሎ ይሰማል ያኛው ይሻላል እያለ የሚጨነቀው ሕዝባችን፡ ከዚህ ጭንቀቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በማይታሰብ ምህረት ያገኝ ዘንድ፡ አብ እንደፈቀደው በክርስቶስ በማመንና በመናዘዝ ይቅርታውን ከሠላም ጋር እንዳጹቀበል፡ ለጻድቃን ለሰማዕታት ለምንላቸው ስጦታ የሰጠ ወንጀሉ ተደብቆለት መንግሥተ ሰማያት ይገባል በማለት እያስተማሩ ይህ የዋህ ሕዝብ ምህረት ሳያገኝ ወደ ሞት ለመንዳት እንደሆነ ታውቆባቸዋል።

ጽንስ ማስወረድ ብቻ ሳይሆን ተአምረ ገ/መ/ቅ የተባለው መጽሐፍ ልጅን በመስጠት ችሎታ እንዳለው በዚሁ መጽሐፍ ሰፍሯል:: « እኔ እግዚአብሔር ማሕጸንን የምዘጋ የምከፍት ነኝ » የሚለውን የልዑል ቃል በመንጠቅ ለገ/መ/ቅ ሰጥተውት ይገኛሉ::

ጽንሷን እንዳስወረዱላት የሰማች አንዲት መካን ሴት እኔም በገብረ መንፈስ ቅዱስ ገድል መጽሐፍ አምናለሁ እስከ ዕለተ ሞቴም ድረስ መታሰቢያውን ( ዝክሩን ) አደርጋለሁ ለዘላለምም ባሪያው እሆናለሁ ብላ የገድሉን መጽሐፍ ተሳልማው ሄደች ወዲያው ሴቲቱ ጸነሰች ገ/መ/ቅዱስም ልጅን ሰጣት ይላል ::  ግልጥ ዓላማቸው የእግዚአብሔር ስምና ሥራ እንዳይታሰብ እንዳይታወቅ መሆኑን ተረድተን ይሆን ? ሌላው በጽሑፋቸው ላይ ትኩረት የተደረገባቸው ጽሑፎች « መታሰቢያውን ማድረግ (ማለትም ጠላና እህል ደግሶ ማክበር ማለት ነው) የሚለው ቃል ነው:

## ክርስትና ክር ( ማተብ ) አይደለም

እኔ ማተቤን አልበጥስም የሚለው ንግግራችን በሁላችን ዘንድ የታወቀና የተለመደ ነው:: በእኛ ዘንድ ማተብ ( በአንገታችን ላይ ያለ ክር ) ክርስትና ከሚለው ቃል ጋር አንድ ነው:: ከዚህም የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የሚለው መንፈሳዊ ትርጉም በ10 ሣንቲም ገዝተን ባሰርነው ክር ተተክቶ እያንዳንዱ ምዕመን ክርስትናን ለመኖር ሳይሆን አንገቱ ላይ ያለውን ክር እንዳይበጠስ ይጠነቀቃል::

ማተብ በቤተክርስቲያናችን አመጣጥ በአፈ ታሪክ እንደሚነገርለት በዘመኑ ክርስትናን እያመኑ የተቀበሉት ሰዎች ይፈጸምላቸው የነበረውን የጥምቀት ሥርዓት ጥልቅ በሆነ ግንዛቤ ወይም ትምህርት ሳይወስዱ ስለነበር አንድ አመንሁ ያለ ሰው እየደጋገመ ይህን የውኃ ጥምቀት ሥርዓት እየፈጸመ ያዩ አጥማቂዎች ይህን ለመለየት ሲሉ በተጠማቂው አንገት ላይ (አንዳንዶች እጅ ላይ ይላሉ ) ክር በማሰር ለቤተ ዘመድ ምልክት እንደሆናቸው ይነገራል::

የውኃ ጥምቀት መውሰድና አለመውሰዱ ይለይበት ዘንድ ምልክት ሆኖ የቆየው ክር እየቆየ ሲመጣ ክርስትና የተባለውን መንፈሳዊና በመለኮት ፈቃድ

የተሰጠውን ሕይወት  በመተካት ክርስትናዬ ከማለት ይልቅ ማተቤ የሚለው በማየሉ ዛሬ ስለ ክርስቶስ ዕውቀት አልባ የሆነው ከ85 በመቶ ሕዝባችን ክርስቶስ የሌለው ማተብ ግን ያለው ነው::

ይህም እውቀት በአልተማረው ሕዝባችን ብቻ ሳይሆን ዘመን አመጣሾቹንም በቀለም ትምህርታቸው ከፍ ያሉ ለሀገር ለወገን ይጠቅሙ ዘንድ ተስፋ ተጥሎባቸው የነበሩና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተመረቁትንም በመማረኩ ሥጋዊ እውቀታቸውን ለዚሁ ለቀደምት መናፍቃን ትምህርት በማስገዛት ለማተብ ( ለክሩ ) መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ፈልገው ሕይወት ሊዘሩበትና ለክር ያለው የሕዝባችን የተሳሳተ ትምህርት እንዲቀጥል እውቀታቸውን ገንዘባቸውን ጉልበታቸውን እያፈሰሱ ይገኛሉ::

አዲሶቹ መናፍቃን ማተብ ( ክሩ ) በኤፌ 4:30 ና በኤፌ 1÷13 ያለውን ታትማችኋል የሚለውን ቃል በዘመነ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ሲሆን ዛሬ ደግሞ በማተብ ( በክር ) እንደተተካ ይተርካሉ፡ አባቶቻችን በአንብሮተ ዕድ ( እጅን በመጫን ) ሀብተ መንፈስ ቅዱስን በአማንያን ላይ ያሳድሩ ነበር ዛሬ ግን ያ ቀርቶ በሜሮን ሆኗል እንደሚሉት ተረት ዓይነት መሆኑ ነው::

በመሠረቱ ማተብ ( ክር) በሐዋርያት አባቶቻችን የተሰጠ ትምህርት ሳይሆን ከላይ እንደገለጥነው ዛሬ ድምጽ ለመስጠት ስንወጣ ጣቶቻችንን በቀለም በመቀባት አንድ ሰው ከአንድ ድምጽ በላይ ሌላ ድምጽ እንዳይኖረው ለመለየት እንደሚጠቀሙበት ያልተጠመቀውን ከተጠመቀው ለመለየት የነበረ ምልክት እንጂ ክርስቲያንነት እንዳልሆነ ዛሬም አንዳንድ የደጋግ አባቶችና መምህራን ቅሪቶች ይመሰክራሉ::

ክርስቲያን ወይም የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን « መንፈሱ ከመንፈሳችን ጋር ተባብሮ ያስረዳናል እንጂ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ክሮችን ገምደ በአንገት ማሰር ወይም ቅርጻ ቅርጽ ማንጠልጠላችን አይደለም:: ዛሬ ባለንበት ዘመን እንኳ ክራችንን ( ማተባችንን ) ማጣት ማለት ከክርስቶስ ከመለየት እጅግ የበለጠ አድርገው በመሳል ሕዝቡ በእግዚአብሔር ቃል ተሞልቶ በማይታየው ግን ሕያው በሆነው በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም እንዳይታተም ለማደናገር ይህን ክፋዎች ከምልክትነት ወደ ሃይማኖትነት የለወጡትን ክር ታላቅነትና አስፈላጊነት የገድለ ገ/መ/ቅ ገድል ነው በሚባለው መጽሐፍ እንዲህ ጽፈውታል::

ተአምር

1. ልመናው ይደረግልን በረከቱ ይደርብንና አቡነ ገ/ መንፈስ ቅዱስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው ። ለዘላለሙ አሜን።
2 .አንድ ሰው የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን መታሰቢያ በሚያደረግበት ቀን አዲስ ማተብ በራሱ ላይ አድርጎ መጣ በመጋቢት አምስት ቀንም የአባታችን የገብረ መንፈስ ቅዱስ መታሰቢያ ወደ ሚደረግበት ሲሄድ ጭላት ( ጭልፊት ) መጥቶ ያን ማተብ ከራሱ ላይ ወሰደበት።
3. ያም ሰው በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ተማጽኛለሁ ማተቤን አትውሰድ አለው ጭላቱም እንቢ ብሎ ያቺን ማተብ ወሰደበት ።
4. ሰውዬውም ወደ ቤተክርስቲያን ሄዶ ሥጋውንና ደሙን ከተቀበለ በኋላ ወደ ቤቱ ተመልሶ ሲሄድ ያን ጭላት በመንገድ ሞቶ አገኘው ማተቡም በአንገቱ ላይ ነበር።
5. ያም ሰው ማተቡን ወስደ የአባታችንን ሥራ እያደነቀ ሔዶ ለሰው ሁሉ ተናገረ።
6. ልመናው ይደረግልን በረከቱ ይደርብን ለዘላለሙ አሜን ።ይላል ።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ምንድን ነው ? የዚያ ሰው ማተብ ( ክር ) ከክርስትናው ጋር ( ያውም ሰውየው ክርስቲያን ከሆነ ነው ) ምን አያያዘው ?

ገድለ ሐዋርያትን ስንመለከት የተጻፈላቸውና እግዚአብሔርም የሚደሰትበት ገድላቸው « ሰው በክርስቶስ ማመኑ ብቻ እንደሆነ » በየስማቸው የተጻፈውን መመልከት በቂ ነው ። ( መጽሐፍ ቅዱስ ) እንዲያውም ሐዋርያት አባቶቻችን « እኛ የተረገምን ሆነን ወገኖቻችን በክርስቶስ በማመን እንዲድኑ ነው » በማለት የልባቸውን ናፍቆት ከእንባ ጋር ጽፈውልናል።( ሮሜ 9÷ 3)

ጻሐፊዎቹ ቅዱስ እያሉ የሚጠሩት ሰው ግን ሠራው የተባለው ገድሉ ክር በማሳሰር ፣ ጽንስ በማስወረድ የሰለጠነ እንደነበር ጻሐፊዎችን መንፈስ ቅዱስ ልባቸውን ጸፍቶ አፋቸውን ከፍቶ አናግሯቸዋል ።

በተለይ የገድሉን መጽሐፍ ለምትመለከቱ ሰዎች ሰውየው አደረጉት የተባለው ተአምር «መታሰቢያቸውን ለሚያደርጉ» ሰዎች የሚያደርጉት አድልዎ ነው። በዚህም ሥራቸው እግዚአብሔር እንኳ በፍጥረቱ ላይ የመበየን ሥልጣን እስከማያገኝ ድረስ ፈጥነው በመድረስ « ይች ነፍስ ትማርልኝ » እያሉ ያስምራሉ ይሉናል።

ሕጻናት ከገደል ላይ ወድቀው ሲሞቱ ከዚያ ውስጥ የገ/መ/ቅዱስን መታሰቢያ ( ጸበል ጸዲቅ ) ያደረገች ሴት ልጇ ከሞተ ከሦስት ሰዓት በኋላ እንደተነሳ፣ ( 8ኛ ተአምር ) በግና በሬ ይዞ ሲሄድ የነበረውን ሰው አንበሶችና ነብሮች ከሰውየው ቀምተውት ወደ ጫካ በገቡ ጊዜ ገ/መ/ቅዱስ አንበሳውንና ነብሩን የቀሟቸውን በግና በሬ ሳይበሏቸው እንዲጠብቋቸው አድረገው ከ1 ዓመት በኋላ ቤተመቅደስ ወስደው ለዚያ ሰው እንደመለሱ ይናገራል ። ሰውየውም የገ/መ/ቅዱስን መታሰቢያ በማድረግ የታወቀ ነበር (9ኛ ተአምር) ።

# ፈውስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወይስ በጠላ ጋን ?

ለመጽሐፍ ቅዱስ እንግዳና ባእድ የሆነው የቤተክርስቲያናችን ምዕመን በካህናቱ ላይ በነበረው የየዋህነት አመኔታ ካህናቱ ያሉትን ሁሉ እንደ እግዚአብሔር ድምጥ እየተቀበለ የኖረ በመሆኑ አባቶቹ የሚላቸው ካህናቱ የሚያዙትን የሚናገሩትን፣ የሚያስተምሩትን ማናቸውንም ቃል የሚመዝንበት፣ የሚለካበት መለኪያ ስለሌለው እስከ ዛሬ ሲፈጽማቸው የኖራቸው ልማ ዶችና ሥርዓ ቶች ትምህርቶችና ወጎች ከተደበቁበት የግእዝ ቋንቋ በእግዚአብሔር ፈቃድ እየተገለጡ ህዝብ በሚያውቀው ቋንቋ በመተርጎማቸው ከምንኩራባቸው ይልቅ የምናፍርባቸው ከምንፎክርባቸው ይልቅ አንገት የምንደፋባቸው የሆኑ በእግዚአብሔርም ፊት ተጠያቂ የሚያ ደርጉን በደሎች መሆናቸው መታወቅ ጀምረዋል።

ስለ ስግደት፣ ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ጽድቅ ስለ ቅድስና ፣ስለ ዘላለም ሕይወት፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት ፣ስለ ሲኦል፣ ስለ ኩነኔና እንዲሁም ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ስለ እምነትና ንስሐ ስለ መላእክት ሆነ ስለ ቅዱ ሳን ሰዎች ያለን ትምህርት ሆነ አመለካከት በመጽሐፍ ቅዱስ ሲታይ ከተጠያቂነት ሊያወጣን የማይችል መሆን ብቻ ሳይሆን አንዳንዱ ግብራችን ዐረ ክርስትና፣ ፀረ ክርስቶስ ፣ ጸረ መጽሐፍ ቅዱስና ፀረ ቤተክርስቲያን ሆኖ ተገኝቷል።(ስለ እያንዳንዱ ጉዳይ የዝግጅት ክፍላችን በየጊዜው እያዘጋጀ ወደፊት ያቀርብልናል )

በዛሬው ጽሑፋችን ገብረመንፈስ ቅዱስ በተባሉ ሰው ስም ከተጻፈው መጽሐፍ በክፉዎች የገባውን ፀረ ክርስቶስና ክርስትና የሆነውን አንድ ክፍል

እናያለን። በሥጋ የተገለጠው አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ ስለ ጸሎት ሲያስተምር « አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል እስካሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበላላችሁ » ( ዮሐ 16፡ 24 ) « በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ »(ዮሐ14:14) በማለት ስለማንኛውም ጉዳዮቻችን ስንጸልይ በስሙ ማለትም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንድንጸልይ አስተምሯል ፡

ሐዋርያትም ይህን የጌታን ቃል በመቀበል « በቃል ሆነ በሥራ የምታ ደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድ ርጉት (ቆላ3:17 ) በማለት የተቀበሉትን የጌታን ትእዛዝ አስተላልፈውልናል ።በእውነተኛይቱ የክርስቶስ ቤተክር ስቲያንም ይህ ትምህርትና ሥርዓት ይከናወን ነበር።

በገድለ ሐዋርያቱ (የሐዋርያት ሥራ እየተባለ የሚታወቀው መጽሐፍ ማለታችን ነው ) በምዕራፍ 3 :1 - 10 እንዲህ የሚነበብ የሐዋርያት ተአምር ይነበባል። በቤተመቅደስ መመላለሻ መንገድ ዳር ተቀምጦ ገንዘብ በመለመን የነበረ አንድ ሽባ ሰው በአንድ የጸሎት ቀን ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በዚያ ሲያልፉ አይቶ ገንዘብ ይሰጡት ዘንድ ሽቶ ወደ እነሱ አይኖቹን በአቀና ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የሰውየውን አንዳች መፈለግ ተመልክቶ እንዲህ አለው « ብርና ወርቅ የለኝም ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ » አለው ። ይህንም ባለው ጊዜ « እግሩና ቁርጭምጭምቱ ጸና ወደ ላይ ዘሎም ቆመ ይመላለስም ጀመረ » ይላል።

ይህን የሰሙ አለቆችና የመቅደስ አዛዦች ሰዱቃውያን ሽማግሌዎችም ጸፎችም ሊቀ ካህናቱ ቀያፉ እስክንድሮስም የተባሉ እምአዝማደ ካህናት ( የካህናቱ ወገኖችና ዘመዶች ) በሙሉ ተሰባስበው ቅዱስ ጴጥሮስንና ዮሐንስን በፊታቸው አቁመው « በምን ኃይል ወይም በማን ሥም እናንተ ይህን አደረጋችሁ ? በማለት በጠየቋቸው ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ተነስቶ መንፈስ እግዚአብሔርን ተሞልቶ :-

« እናንተ የሕዝብ አለቆችና ሽማግ ሌዎች እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰው ስለተደረገው መልካም ሥራ ይህ በምን እንደዳነ ብንመ ረምር እናንተ

በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን ባስነሳው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይህ ደህና ሆኖ በፊታችሁ እንደቆመ ለእናንተ ለሁላችሁ የታወቀ ይሁን በማለት መስክሯል:: ( የሐዋ 4+ 1- 12 )

የእውነተኛዎቹ ሐዋርያት ገድልና ተአምር እንዲህ ተጽፎ እያለ በእኛዎቹ ሰዎች የተደረሱ ወይም ተደርሰው ከውጭ መጡልን በሚባሉ በስመ ቅዱሳን ተሸፍነው ተአምር ዘእገሌ ፣ድርሳነ ዘእገሊት እየተባሉ በሚጠሩ መጻሕፍት ውስጥ ግን የእውነተኛይቱን ቤተክርስቲያን ገድልና ተአምር የሚቃረን የእግዚአብሔርንም ፈቃድና ውዴታ የሚጋፋ ምዕመናንንም ባእድ አምልኮ የሚያስተምር ባዕድ ነገር ታጉርባቸው ይገኛሉ:::

ተአምረ ገብረ መንፈስ ቅዱስ :-

በስእል ከሚማጸኑ በስዕልም ፊት ከሚጸልዩ ቤተሰብ መካከል የተወለዱት ገብረ መንፈስ ቅዱስ እናታቸው በስዕሉ ፊት ቆማ ስዕሉን እያናገረች በምትጸልይበት ጊዜ ከስዕሉ በወጣ ቃል (ትንቢት ) መሠረት ሹመታቸው እንደ መልከ ጼዴቅ የሆነ ካህኗ በቅድስና በፍጹምነት ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር የሚተካከል በግብጽ በረሃ 300 ዓመት በኢትዮጵያ 260 ዓመት የኖሩ ስለ ኢትዮጵያ የጸለዩና እግዚአ ብሔር አሥራት አድርጎ የሰጣቸው በተለይም ለጎጃም ሕዝብ ለ100 ዓመት ቡዳነቱ እንዲለቀው ጸልየው ያስማሩት ሰው እንደሆኑ በእጃችን የሚገኘው ገድላ ቸው ይተርካል:

በአፈ ታሪክም የተወለዱበት ቀን ፆም በመሆኑ እናታቸው የጡቷን ወተት ልታጠባ ቸው በፈለገች ጊዜ በፆም ቀን ወተት መጠጣትየዘገነናቸው ገብረመንፈስቅዱስ ለእናታቸው በፆሙ ወተት መጥባት እንደ ማይፈልጉ የተናገሩ ሰው ናቸው እየተባለ በሰፊው የሚሰበክ ላቸው ናቸው :

የእኚህ ሰው ተአምር ነው ተብሎ በገድላቸው ላይ የተደረሰላቸው እንዲህ ይነበባል:

## ዐሥራ አንደኛ ተአምር

፩ ልመናው ይደረግልን በረከቱ ለዘላለሙ ይደርብንና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያደረገው ተአምር ይህ ነው ::
፪ በናዖድ ንጉሥ ዘመነ መንግሥት ለአንዲት ሴት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ያደረገላት ተአምርና ድንቅ ሥራ ይህ ነው::
፫ ሕፃን ልጇ ከሞተና ነፍሱም ከሥጋው ከተለየች በኋላ በአባታችን ጸሎት በማመን ማኅበር ወደ ሚጠጡበት በድኑን (አስከሬኑን) ወሰደችው
፬ በዚያ የማኅበር ቤትም ጋን ተቀምጦ አገኘች ጋኑን አስተካክላ በምድር ላይ አቆመችው « አባ አባታችን አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በጸሎትህ ተማፅኛለሁ ማኅበርህ በሚሠራበት በዚህ ጋን ( ለገብረ መንፈስ ቅዱስ ዝክር ጠላ በሚጠመቅበትጋን ማለት ነው ) ልጄን አስነሳው ብላ ሕፃኑን በጋኑ ውስጥ ጨመረችው::
፭ ልጁም ያን ጊዜውኑ ተነስቶ ከጋኑ ውስጥ እንዳለ ሙኽ ጡቷንም አውጥታ ሰጠችውና ጠባ::
፮ ልመናው ይደረግልን በረከቱ ለዘላለሙ ይደርብን አሜን:: በማለት ይናገራል::

ጌታችን ሆነ ሐዋርያቱ ለማንኛውም ችግራችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አድርጉ ሲሉን መናፍቃኑ ግን ለገብረ መንፈስ ቅዱስ ዝክር ጠላ በሚጠመቅበት ጋን ሙት ማስነሳት ይቻላል በማለት የጌታ ስም እንዳይጠራ ይህን የክህደት ጽሁፍ ተአምር በማለት ጽፈውታል:: አንባቢ ያስተውል እንደተባለ ባለፈው ያለማወቅ ጊዜያችን የበደልነው ስለሚበቃ ከእንዲህ አይነት ወንጀል ራሳችንን ብሎም ቤተሰቦቻችን በመጠበቅ ለቤተክርስቲያናችን ፈውስ እናገልግል:: ፈውስ ሆነ ከሙታን መነሳት በክረስቶስ ስም ነው ወይስ በጠላ ጋን